66 orange

በአማራ ብሔራዊ ክልል
የመንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች/መያድ/
የትብብር መመሪያ
ረቂቅ

ከጥር 27 - 29/1992 ዓ/ም
ለሚካሄደው የመንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች
ክልላዊ ኮንፈረንስ ውይይት የቀረበ ረቂቅ መመሪያ

አብከመ አመዝኮ
ባሕር ዳር

CCRDA

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

የመንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች /መያድ/

የትብብር መመሪያ

CGRDA

ለመንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ክልላዊ ኮንፈረንስ

ከጥር 27-29/1992

ውይይት የቀረበ ረቂቅ መመሪያ

አ/ብ/ክ/መንግሥት

አመዝኮ

ባህር ዳር

ጥር 1992

ማ ው ጫ

መ ግ ቢ ያ

I . መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ..... 1 - 7

1.1 የመያድ መለያዎች

1.2 መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች መርሆዎች

1.3 የመያድ የሥምሪት መስኮች

1.4 በመያድ ትኩረት የሚሰጣቸው ዋና ዋና ተግባሮች

II. መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ህጋዊነትና ሥምሪት ..... 7 - 11

2.1 የመያድ ሕጋዊነት

2..2 የመያድ የምዝገባ መስፈርት

2.3 የመያድ የሥራ ሥምሪት ጥያቄና የአፈጻጸም ሂደት

III. የኘሮጀክት ዝግጅት ማጽደቅና ስምምነት ሂደቶች 11-23

3.1 የፍላጐት ጥናት/የኘሮጀክት መረጣ

3.2 የኘሮጀክት ሠነድ ዝግጅት

3.3 የኘሮጀክት ማጽደቅ ሂደት

3.4 የኘሮጀክት ስምምነት

IV የመያድ ኘሮጀክት አፈጻጸም ሂደት 23- 29

4.1 የኘሮጀክት ስምምነት ማክበር

4.2 የኘሮጀክት ዓመታዊ የድርጊት መርሃ ግብር

4.3 በኘሮጀክት አፈጻጸም የሕዝብ ተሳትፎን ማረጋገጥ

4.4 የኘሮጀክት ሐብት አጠቃቀምና አስተዳደር

4.5 የኘሮጀክት ሠነድ ማስተካከል

4.6 የኘሮጀክት ጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄ

CCRDA

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
የመንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች (መያድ)
የትብብር መመሪያ

መ ግ ቢ ያ

ኢትዮጵያ ከደርግ መንግሥት ውድቀት ማግሥት በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ጐዳና የምትጓዝ አገር በመሆኗ የሕዝቡን የኑሮ ደረጃ ለመለወጥ ለልማት በሰጠችው ትኩረት ሕ/ሰቡና መንግሥት የሚያካሂዱትን የልማት ጥረት ለማገዝ በርካታ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በተለያዩ የሐገሪቱ ክፍሎች ልዩ ልዩ የልማት ኘሮጀክቶችና ኘሮግራሞች ቀርፀው በተግባራዊ እንቅስቃሴ ላይ ተሰማርተዋል፡፡

ዓለም ዓቀፍ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችም ሆነ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓቱን ለውጥ ተከትለው ወደ መድረክ የመጡት አገር በቀል መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በአሁኑ ወቅት በዕለት ዕርዳታ አቅርቦት ብቻ ሳይወሰኑ ለልማት ተግባር በሰጡት ትኩረት በግብርና ልማት፣ በማኅበረ-ኢኮኖሚያዊ መሠረተ ልማት፣ በአካባቢ ጥበቃና በልዩ ልዩ ማኅበራዊ አገልግሎቶችና የአቅም ግንባታ መስኮች አበረታች ተግባር በማከናወን ላይ መሆናቸው በሐገሪቱ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ውጤታማ የልማት ሥራዎችን በብቃት መተግበር የሚችሉበት ምቹ ሁኔታ መፈጠሩን ያረጋግጣል፡፡

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሕ/ሰቡን የኑሮ ደረጃ ለመለወጥ የተነደፈውን የልማት መርሃ-ግብር ተግባራዊ ለማድረግ ሕ/ሰቡና መንግሥት የሚያደርጉትን ጥረት ለማገዝ በክልሉ የሚንቀሳቀሱት ዓለም ዓቀፍና አገር በቀል መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በልዩ ልዩ የልማት ኘሮጀክቶች፣ በማኅበራዊ ኘሮግራሞችና በአቅም ግንባታ መስኮች ተሰማርተው የልማት አጋርነታቸውን በማረጋገጥ ላይ ይገኛሉ፡፡ ይህ የመንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እንቅስቃሴ መንግሥት ያወጣውን የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ፖሊሲ ተግባራዊ ለማድረግ እያበረከተ ያለው እገዛ በአዎንታነት የሚታይ ነው፡፡

በክልሉ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የመንግሥት አካላት ትብብር የእስከአሁኑ ሂደት የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ብሔራዊ ፖሊሲን መሠረት አድርጐ በተዘጋጀው የመያድ አገር አቀፍ መመሪያ /Guideline for NGOs Operation in Ethiopia / መሠረት ሲመራ የቆዬ ቢሆንም በክልሉ ነባራዊ ሁኔታ የተዘጋጀ የመንግሥት አካላትና የመያድ የትብብር መመሪያ አልነበረም፡፡ በአሁኑ ወቅት በክልሉ ከሚታዬው የመያድ እንቅስቃሴ ስፋትና ካለፉት የጋራ እንቅስቃሴዎቸችን ልምዶች ስንነሳ የመያድና የመንግሥታዊ አካላት የልማት ትብብር ክልላዊ የትብብር መመሪያ የሚያስፈልገው መሆኑ ታምኖበታል፡፡

CCRDA

የትብብር መመሪያው ዋነኛ ዓላማ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች (መያድ)በክልሉ ማኅበረ-ኢኮኖሚያዊ ልማት መስኮች ያላቸውን አጋርነት በማጠናከር ሕ/ሰቡን የልማት ተጠቃሚ ማድረግ ሲሆን፣ የትብብር መመሪያው ይዘት በዋነኛነት፡-

- የመያድ መርሆዎች፣ ሕጋዊነትና የሥምሪት መስኮች፣
- በመያድ ኘሮጀክቶችና ኘሮግራሞች የፍላጎት ጥናት፣ በኘሮጀክት ቀረጻ፣ በኘሮጀክት ስምምነት፣ በኘሮጀክት መተግበር / Implementation/ ፣ በኘሮጀክት ግምገማና ርክክብ ሂደት የሚኖር አፈጻጸም ፣
- የሕ/ሰቡን ችግሮች ደረጃ በደረጃ ለመቅረፍ በሚደረገው ጥረት የመያድን የኘሮጀክት ሐብት፣ የመንግሥት አካላትን ቁሣዊ፣ ቴክኒካዊና አስተዳደራዊ ድጋፍና የሕ/ሰቡን ዙሪያ መለስ ተሣትፎ አዋህዶ በብቃትና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመጠቀም በልማት አጋሮች (መንግሥት፣ መያድና ተጠቃሚው ሕ/ሰብ) መካከል ሊኖር የሚገባውን ቅንጅታዊ አሠራር፣ የእያንዳንዳቸው ተግባርና፣ ኃላፊነትና ተጠያቂነት፣
- የመያድ የኘሮጀክት አፈጻጸም ግምገማና ሪፖርት ሥርዓትን
- የመንግሥት አካላትንና የመያድን የልማት አጋርነት ለማጠናከር በየደረጃው በሚቋቋሙት የትብብር ኮሚቴዎች ተግባርና ኃላፊነት ወዘተ ... ላይ ያተኩራል።

CCRDA

1. መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች (መያድ)

መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች (መያድ) ለትርፍ ያልተመሠረቱ፣ በራሳቸው መንገድ ገንዘብ፣ ቁሣቁሶችና የሰው ኃይል በማስተባበር በህ/ሰቡና በመንግሥት ያልተቃለሉ ችግሮችን ለመቅረፍ በማኅበረ-ኢኮኖሚያዊ አገልግሎትና ልማት መስክ አስተዋጽኦ የሚያበረክቱ ሕጋዊ ድርጅቶች ናቸው::

1.1 የመያድ መለያዎች

መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የተቋቋሙበት ዋነኛ ዓላማ ተመሳሳይ በመሆኑ ለያይቶ ማስቀመጥ አስቸጋሪ ቢሆንም አንዳንድ አጠቃላይ መመዘኛዎችን በመውሰድ በአገራችንና በአማራ ብሔራዊ ክልል የሚሰሩትን መያድ መነሻ በማድረግ እንደሚከተለው ከፋፍሎ ማየት ይቻላል::

1.1.1 በአመሰራረታቸው /Classification by Origin/

በአማራ ብሔራዊ ክልል የሚንቀሳቀሱት መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አገር በቀልና ዓለም ዓቀፍ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተብለው በሁለት ሊከፈሉ ይችላሉ ::

1.1.1.1 አገር በቀል መያድ /National/local NGOs/

መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በአንድ አገር ውስጥ ተመሥርተው ለህ/ሰቡ የሚሰጡት ማኅበረ-ኢኮኖሚያዊ አገልግሎት በተመሠረቱበት ሐገር ውስጥ ብቻ የተወሰነ ከሆነ አገር በቀል መያድ /Nationlal/local NGOs/ ተብለው ይጠራቁ:: በአሁኑ ወቅት በአገር አቀፍ በክልል አቀፍ ወይም በተወሰነ አካባቢ እየተንቀሳቀሱ ያሉ አገር በቀል መንግሥታዊ ያለሆኑ ድርጅቶች የተመሠረቱትና ማኅበረ-ኢኮኖሚያዊ አገልግሎት የሚሰጡት በኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ በመሆኑ አገር በቀል መያድ የሚል ስያሜ ተሰጥቷቸዋል::

1.1.1.2 ዓለም አቀፍ መያድ /International NGOs/

በተመሠረቱበት ሐገር ብቻ ሳይወሰኑ በተለያዩ ሐገሮች ለህ/ሰቡ ማኅበረ ኢኮኖሚያዊ አገልግሎት የሚሰጡ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ዓለም ዓቀፍ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች/መያድ/ ተብለው ይጠራሉ:: በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ የሚንቀሳቀሱት ዓለም ዓቀፍ መያድ የተመሠረቱት በሌሎች ሐገሮች ሆኖ ነገር ግን በኢትዮጵያ ህ/ሰብ ውስጥ ራሳቸውን ችለው፣ ከአገር በቀል መያድ ጋር ተቀናጅተው ወይም የሴክተር መ/ቤቶችን መዋቅር በመጠቀም የሕ/ሰቡን ፍላጐት መሠረት ያደረጉ ፕሮጀክቶችን ለመተግበር የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች ናቸው::

CGRDA

1.1.2 መሥራት በሚፈልጉበት አካባቢ / Classification by Geographic Area/

የተወሰኑ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ችግር ባለበት በየትኛውም የሐገሪቱ ወይም የክልሉ አካባቢ ለመሥራት አገር አቀፍ ወይም ክልል አቀፍ እንቅስቃሴ የሚያካሂዱ ሲሆን፣ አንዳንዶቹ ደግሞ በተወሰኑ አካባቢዎች ብቻ ለመሥራት የተቋቋሙ ናቸው።

1.1.3 የሃይማኖት ይዘት ያላቸውና የሌላቸው /Classification by affiliation/

አንዳንድ መያድ ሃይማኖታዊ ይዘት የሌላቸው ሲሆን አንዳንዶቹ ደግሞ የሃይማኖት ይዘት ያላቸው ሆነው ዕምነታቸውን ለማስፋፋት አመቺ በሆኑ አካባቢዎች ለመስራት የሚፈልጉ ናቸው።

1.1.4 በተሳትፎአቸው ዓይነት /Classification by Involvement/

አብዛኛዎቹ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የፕሮጀክት ፈጻሚዎች (Project Implementing NGOs) ሲሆኑ፣ ጥቂቶች ደግሞ የፕሮጀክት ማስፈጸሚያ በጀት የሚያቀርቡ (Funding NGOs) ናቸው።

1.1.5 በሚያከናውኑት ስራ /Classification by Programme Orientation/

መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አብዛኛውን ጊዜ በልማትና በዕለት ዕርዳታ ስራ ላይ ይሰማራሉ።

1.1.5.1 የልማት ቅኝት ያላቸው መያድ /Development oriented NGOs/

በልማት ሥራ ላይ የሚሠማሩት መያድ አብዛኛውን ጊዜ በተፈጥሮ ሃብትና በሰው ኃይል ሃብት ልማት፣በግብርና፣ በጤና ወዘተ ... መሰረተ ልማት ሥራ ላይ ትኩረት ሰጥተው የሚሠማሩ ከሆነ የልማት ቅኝት ያላቸው መያድ /Development oriented NGOs/ ተብለው ይጠራሉ።

1.1.5.2 የዕለት ዕርዳታ አቅርቦት ቅኝት ያላቸው መያድ /Relief oriented NGOs/

አብዛኛውን ጊዜ በዕለት ዕርዳታ አቅርቦት የሚሠማሩ መያድ በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ ችግር ምክንያት ራሳቸውን መርዳት ላልቻሉት ወገኖች የምግብ ዕርዳታና ተመሳሳይ አገልግሎት በመስጠት ላይ ያተኮረ እንቅስቃሴ ያላቸው በመሆናቸው የዕለት ዕርዳታ አቅርቦት ቅኝት ያላቸው መያድ /Relief oriented NGOs/ ተብለው ይጠራሉ።

CCRDA

1.2 መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሚመሩባቸው መርሆዎች ፣

መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ግንኙነት፣ የሚሰጡት አገልግሎት እና የሚያከናውኑት ስራ በመርህ ላይ የተመሰረተ መሆን ይኖርበታል። አንዳንዶቹ መርሆዎችም እንደ ስነ ምግባር መመሪያ ሆነው ሊያገለግሉ ይችላሉ። በዚህም መሰረት መያድ በሚያከናውኗቸው ስራዎች ሁሉ ሊመሩባቸው የሚገቡ መርሆዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

1.2.1 ተጠያቂነት /Accountability/ መያድ በገቡት ውለታ መሰረት ግዴታዎቻቸውንና የተጣለባቸውን እምነት ካልተወጡ በተጠቃሚ ወገኖች፣ በህብረተሰቡ ሥራው በሚመለከታቸው ሴክተር መ/ቤቶች፣ በመስተዳድር አካላትና በለጋሽ ድርጅቶች ተጠያቂ ይሆናሉ።

1.2.2 የመወሰንና በራስ የመተማመን አቅምን ማሳደግ /Empowerment/

የኘሮጀክት ተጠቃሚዎችን፣ የአካባቢውን ሕ/ሰብና ስራው የሚመለከታቸውን የሴክተር መ/ቤቶች አቅም በመገንባት በራስ መተማመንን በማጐለበት የመወሰን አቅማቸውን ማጠናከርና፣ ራሳቸውን በማስቻል የአደጋ ተጋላጭነትንና የጥገኝነት ችግሮችን መቅረፍ፣

1.2.3 አድልዎ አለማድረግ /Indiscrimination/

ዕድሜን፣ጸታን፣ጐሣን፣ ብሄረሰብን የፖለቲካ ልዩነትን፣ ሃይማኖትን፣ የትውልድ አካባቢንና፣ አካል ጉዳተኝነትን ወዘተ ልዩነት ያላደረገ አገልግሎት መስጠት፣

1.2.4 ተሳትፎን /Participation/ ማረጋገጥ

በፍላጎት ጥናት /ኘሮጀክት መረጣ፣ በኘሮጀክት ዝግጅት፣ በኘሮጀክት አፈጻጸምና ግምገማ ሂደት የኘሮጀክት ተጠቃሚዎች፣ የሚመለከታቸው የሴክተር መ/ቤቶችና ሌሎች አግባብ ያላቸው ሁሉ ነፃና ግልፅ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ማድረግ፣

1.2.5 በጋራ መስራት /Partnership/

ከመያድ፣ ከመንግስት፣ ከህብረተሰቡ፣ ከህብረተሰቡ ድርጅቶችና ሌሎች ሲቪል ድርጅቶች ጋር እውነተኛና መግባባት የተሞላበት ግንኙነት በመፍጠር ዘላቂነት ያለው ልማት ለማምጣት ጥረት ማድረግ፣

1.2.6 ሃብትን በአግባቡ /በቁጠባ/ መጠቀም /Cost effectiveness/

ውስን የሆነውን ሀብት በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ዘላቂነት ባለውና በተጠቃሚው ህብረተሰብ ኑሮ ላይ ለውጥ ሊያመጣ በሚችል ውጤታማ ስራ ላይ ማዋል፣

1.2.7 የተመጣጠነ አገልግሎት መስጠት /Proportionality/

የተመጣጠነ አገልግሎትና የኘሮጀክት የስራ አፈጻጸም በማስፈን በተመሳሳይ የችግር ሁኔታ ላይ የሚገኙ ተጠቃሚዎችና ህብረተሰቡ በመያድ ሀብት ላይ እኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፣

CGRDA

1.4.1 <u>የልማት ቅኝት ያላቸውን ኘሮጀክቶች/ኘሮግራሞች መተግበር ወይም በበጀት መደገፍ</u>

በክልሉ የአደጋ ተጋላጭነት መንስዔዎችን በማስወገድ ድህነትንና ኋላቀርነትን ደረጃ በደረጃ ለመቅረፍ መንግሥት ለገጠር መሠረተ ልማት የሰጠውን ትኩረት ማዕከል በማድረግ በመያድ የሚቀርቡ የልማት ቅኝት ያላቸው ኘሮጀክቶች/ኘሮግራሞች በዋነኛነት፡-

- በአካባቢ ጥበቃና ልማት፣
  - ደን ልማት
  - አፈርና ውሃ ጥበቃ
- በግብርና ልማት፣
  - አዝርዕት ጥበቃና ልማት
  - መስኖ ልማት
  - እንስሳት ሐብት ልማት
  - ኤክስቴንሽን አገልግሎት
- በውሃ ልማት፣
  - ንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት
  - የከርሰ ምድር ውሃ ልማት
- በትምህርት አገልግሎት ማስፋፋት፣
  - የተቋማት ግንባታ
  - መደበኛና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት
  - የትምህርት መሣሪያ አቅርቦት፣ የቤተ መፃሕፍት አገልግሎት
- በጤና አገልግሎት ማስፋፋት
  - በተቋማት ግንባታ
  - በመሠረተ ጤና ትምህርት
  - የህክምና መሣሪያዎችና መድሃኒት አቅርቦት
  - ክትባት አገልግሎት
- በገጠር መንገድ ሥራና ጥገና፣
- በሌሎች የሕዝብ ጥሪቶች ግንባታ /public asset building / ተግባር ላይ ቅድሚያ በመስጠት መሰማራት ይችላሉ።።

1.4.2 <u>የሥራ ዕድል በሚፈጥሩ ኘሮግራሞች መሠማራት</u>

መያድ በክልሉ የተለያዩ አካባቢዎች ለምግብ እህል እጥረት የሚጋለጡ ወገኖች አካባቢያቸውን ሳይለቁ፣ የእርሻ ሥራቸው ሳይቋረጥና ከአካባቢው ማኅበረ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ሳይገለሉ የአካባቢውን ሕዝብና የተጐጅዎቹን የራሳቸውን ተጠቃሚነት

CGRDA

በሚያረጋግጡና የሕ/ሰቡን የልማት ንቁ ተሳትፎ በማጐልበት በሂደት አደጋን የመቋቋም አቅምን በሚገነቡ ጉልበት ተኮር /labour based/ የሥራ ዕድል የሚፈጥሩ ኘሮግራሞችን (EGS) ለመተግበር መሠማራት ይችላሉ፡፡

1.4.3 <u>የመልሶ ማቋቋም ኘሮግራም</u>

መያድ በክልሉ ውስጥ በማንኛውም ጊዜ አደጋ ለደረሰበት ህብረተሰብ ወይም በልዩ ልዩ ምክንያት የግብርና ወይም ሌላ መደበኛ የመተዳደሪያ ሥራቸውን መቀጠል ላልቻሉ ወገኖች ራሳቸውንና ቤተሰባቸውን በተሻለ ሁኔታ መርዳት ወደሚችሉበት ደረጃ ለማድረስ በሚያስችል የመልሶ ማቋቋም ኘሮጀክት ሊሠማሩ ይችላሉ፡፡

1.4.4 <u>የእንስሳት ሐብት ልማት</u>

በክልሉ ተደጋጋሚ ድርቅ በሚከሰትባቸው አካባቢዎች በድርቅና በሌሎች የተፈጥሮ አደጋዎች እየደረሰ ያለውን የእንስሳት ሐብት መመናመን በመግታት አርሶ አደሩን የእንስሳት ሐብት ልማት ተጠቃሚ ለማድረግ የሚደረገውን ጥረት ለማገዝ መያድ ከዚህ በታች በተመለከቱት መስኮች አስተዋጽኦ ማበርከት ይችላሉ፡፡

ሀ) <u>የተሻሻሉ የቤት እንስሳት ዝርያዎች አቅርቦት</u>

መያድ የአርሶ አደሩን የእንስሳት ሐብት ልማት ተጠቃሚነት ዕውን ለማድረግ በሽታ መቋቋም የሚችሉ፣ የሥጋና የወተት ምርታቸው ከፍተኛ የሆነ፣ የስበት ኃይላቸው (ጉልበታቸው) ጠንካራ የሆኑ የተሻሻሉ የእንስሳት ዝርያዎችን ለተጠቃሚ አርሶ አደሮች እገዛ በማድረግ በስፋት መንቀሳቀስ ይችላሉ፡፡

ለ) <u>የቤት እንስሳት ሕክምና አገልግሎት</u>

ክልሉ የተለያየ የአየር ፀባይ ያላቸው አካባቢዎችን ያቀፈ በመሆኑ በልዩ ልዩ የአየር ፀባይ ክልል የሚከሰቱ የእንስሳት በሽታዎች ከእንስሳት ሕክምና አገልግሎት ስፋት ዝቀተኛነት ጋር ተዳምሮ በእንስሳት ሐብት ላይ የሚያደርሰው ጉዳት ቀላል ስላልሆነ መያድ በእንስሳት የህክምና መሣሪያዎችና መድሃኒት አቅርቦት እንዲሁም በእንስሳት ሕክምና ባለሙያ ሥልጠና መስክ የአቅም ግንባታ ኘሮጀክቶችን በመተግበር በመስኩ ያለውን ክፍተት ለመሙላት የሕዝቡን ችግሮች ለመቅረፍ ሰፊ አስተዋጽኦ ማበርከት ይችላሉ፡፡

ሐ) <u>የእንስሳት መኖ ልማት</u>

- የተሻሻሉ የእንስሳት መኖ ዝርያዎችን ማቅረብ
- የእንስሳት መኖ ልማት ዘዴዎችን ለአርሶ አደሩ በስፋት ማስተዋወቅ

CCRDA

መ) <u>የአደጋ ጊዜ የእንስሳት ደህንነት ጥበቃ አገልግሎት መስጠት</u>

መያድ በአደጋ ጊዜ ሊደርስ የሚችለውን የቤት እንስሳት ሐብት መመናመን ለመግታት የእንስሳት ጊዜያዊ የጥበቃ በረቶችን በማስፋፋት ለአርሶ አደሩ የኑሮ መሠረት እጅግ አስፈላጊ የሆኑ የቤት እንስሳትን ከእልቂት ለመከላከል ይችላሉ፡፡

1.4.5 <u>የዕለት ደራሽ ዕርዳታ ማከፋፈል</u>

አደጋ በደረሰባቸው አካባቢዎች አስቸኳይ የዕለት ዕርዳታ ማቅረብ አስፈላጊ መሆኑ በክልሉ የዕርዳታ ኘሮግራም ሲጸድቅ መያድ በዕለት ደራሽ ዕርዳታ አቅርቦት መሠማራት ይችላሉ፡፡

1.4.6 <u>የሕፃናትና አረጋውያን እንክብካቤ ማካሄድ</u>

በአደጋ ጊዜ በሚደርስ ችግርም ሆነ በሕብረተሰቡ ውስጥ አሳዳጊ የሌላቸውን ሕፃናትና ሿሪ የሌላቸውን አረጋውያን ለመንከባከብ የምግብ አገልግሎት ብቻ የሚሰጡ ማዕከሎችንም ሆነ የምግብ፣ የመጠለያና ሌሎች ማኅበራዊ አገልግሎቶች መስጫ ማዕ ከሎችን በማቋቋም አገልግሎት መስጠት ይችላሉ፡፡ የአገልግሎት መስጫ ተቋማት የሚቋቋሙት አሳዳጊ የሌላቸውን ሕፃናት በህብረተሰቡ ውስጥ መንከባከብ የማይቻል ሆኖ አማራጭ ሲታጣና ሁኔታው አስገዳጅ መሆኑ ሲታመንበት ብቻ ይሆናል፡፡

1.4.7 <u>በሁሉም ኘሮጀክቶች/ኘሮግራሞች ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች</u> /<u>cross-cutting issues/</u>

በመያድ የሚቀረው ኘሮጀክቶችና ኘሮግራሞች ለአካባቢ ጥበቃ፣ ለሥነ-ሕዝብና ለጸታ ልማት ተገቢ ትኩረት ሊሰጡ ይገባል፡፡

2. <u>መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ህጋዊነትና ስምሪት</u>

2.1 <u>የመያድ ሕጋዊነት</u>

ሀ. ማንኛውም በመንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅትነት ወይም በልማት ማኅበርነት ተደራጅቶ ለኅብረተሰቡ አገልግሎት ለመስጠት የሚፈልግ ድርጅት ሥራ ከመጀመሩ በፊት ከሚመለከታቸው የማዕከልና የክልል ሕጋዊ አካላት ሕጋዊ ዕውቅና አግኝቶ መመዝገብና የሥራ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡

ለ. አገር በቀል ድርጅቶችም ሆኑ የውጭ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በፌዴራል ፍትህ ሚ/ር ተመዝግበው የምዝገባ ሰርቲፊኬት ሲሰጣቸውና ከፌዴራል አመዝኮ ጋር አኘሬሽናል ስምምነት ተፈራርመው የስራ ፈቃድ ሲያገኙ ወይም ክልላዊ የሆኑ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በክልሉ ፍትሕ ቢሮ ተመዝግበው ከክልሉ አመዝኮ

CCRDA

ጋር ስምምነት ተፈራርመው የሥራ ፈቃድ ሲያገኙ በመንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅትነት ተመዝግበው የመሥራት ሕጋዊነት ይኖራቸዋል።

2.2 <u>የመያድ የምዝገባ መስፈርት</u>

2.2.1 <u>አገር በቀል መያድ</u>

የአገር በቀል መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ምዝገባ በፌዴራል ፍትሕ ሚኒስቴር ወይም በክልል ፍትሕ ቢሮ አማካኝነት ይካሄዳል።

አገር በቀል መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በፍትሕ ሚ/ር ወይም በክልል ፍትሕ ቢሮ ለመመዝገብ ከሚሞሉት የምዝገባ ፎርም ጋር፡-

- የድርጅት/ማኅበር መመሥረቻ ጽሁፍ፣
- የድርጅት/ማኅበር መተዳደሪያ ደንብ፣
- የቦርድ አባላት የሥነ ምግባር ማረጋገጫ (ከሚኖሩበት ቀበሌ)፣
- የቦርድ አባላት የትምህርት ደረጃና የሥራ ልምድ ማረጋገጫ፣
- የፕሮጀክት ፕሮፋይል / project profile/ እና
- የሚሠሩበት ክልል አመዝኮ ድጋፍ

ሲያቀርቡ የሕጋዊነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት (ሰርቲፊኬት) ከፍትሕ ሚ/ር ወይም ከአማራ ብሔራዊ ክልል ፍትሕ ቢሮ ማግኘት ይችላሉ።

2.2.2 <u>ዓለም ዓቀፍ መያድ</u>

2.2.2.1 የዓለም ዓቀፍ መያድ ምዝገባ በፌዴራል ፍትሕ ሚ/ር ይካሄዳል።

2.2.2.2 ዓለም ዓቀፍ መያድ በፍትሕ ሚኒስቴር ሕጋዊ ምዝገባ ለማካሄድ፡-

ሀ. የፍትሕ ሚኒስቴርን የምዝገባ ፎርም መሙላት፣

ለ. ከተመሠረቱበት አገር የተሰጣቸውን የምዝገባ የምስክር ወረቀት ማቅረብ፣

ሐ. የድርጅታቸውን መተዳደሪያ ደንብ፣

መ. የለጋሽ ድርጅቶች የበጀት ማረጋገጫና፣

ሠ. የፕሮጀክት ፕሮፋይል/project profile/ እና

ረ. ፕሮጀክቶቻቸውን ተግባራዊ የሚያደርጉባቸው ክልሎች ድጋፍ ያላቸው መሆኑ ሲረጋገጥ ድርጅቶቹ በኢትዮጵያ በሕጋዊነት ለመሥራት ተመዝግበው የሕጋዊነት የምስክር ወረቀት ይሰጣቸዋል።

2.2.2.3 የፍትሕ ሚ/ር ወይም የአብክመ ፍትሕ ቢሮ የመያድ ምዝገባ ጥያቄ ሲቀርብላቸው የሚመለከተው መያድ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ለመሥራት በሕጋዊነት ለመመዝገብ ባቀረበው ጥያቄ ላይ አስተያዬት እንዲሰጥ ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አመዝኮ በጽሁፍ ይጠየቃል።

CCRDA

2.2.2.4 የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አመዝኮ ከፍትሕ ሚኒስቴር ወይም ከአብክመ ፍትሕ ቢሮ የመያድ የምዝገባ አስተያዬት ጥያቄ እንደቀረበለት ለሚመለከታቸው የዞን አመዝኮ ቅ/ጽ/ቤቶች በመፃፍ አግባብ ያላቸውን የዞን መንግሥታዊ አካላት ሃላብና በፖሊሲ ጉዳዮችም የሚመለከታቸውን ቢሮዎች አስተያየት ያካተተ የመያድ የምዝገባ አስተያዬት በማሰባሰብ ለምዝገባው ያለውን የድጋፍ ወይም የተቃውሞ አስተያዬት ጥያቄው ከቀረበለት ከ20 የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ምላሽ ይሰጣል::

2.3 የመያድ የሥራ ሥምሪት ጥያቄና የአፈጻጸም ሂደት

2.3.1 የመያድ የሥራ ሥምሪት ጥያቄ የሚቀርብለት አካል

ሀ. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን የማስተባበር ኃላፊነት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን ነው::

ለ. በአማራ ብሔራዊ ክልል የመንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሥራ ሥምሪት ጥያቄ የሚቀርብለት አካል የክልሉ አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን ነው::

2.3.2 የመያድ የሥራ ሥምሪት ጥያቄ አቀራረብ

በአማራ ብሔራዊ ክልል የኘሮጀክት ስምምነት በመፈራረም ኘሮጀክት ተግባራዊ ለማድረግ የሚፈልግ ማንኛውም መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት:-

ሀ. በክልሉ ለመሥራት የሚቀርብ ማመልከቻ፣

ለ. ከፍትሕ ሚ/ር ወይም ከአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የፍትሕ ቢሮ የተሰጠውን የምዝገባ ማስረጃ (ሰርቲፊኬት) ፎቶ ኮፒ፣

ሐ. ከፌዴራል አመዝኮ ወይም ከአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አመዝኮ ጋር የተፈራረመበትን ኦኘሬሽናል ስምምነት ፎቶ ኮፒ፣

መ. ድርጅቱ ተግባራዊ ሊያደርገው /ሊፈጽመው/ ስለሚፈልገው ኘሮጀክት ጠቅለል ያለ የኘሮጀክት ኘሮፋይል:-

1. የኘሮጀክቱ ዓይነት/ የሚያቃልለው ችግር፣
2. ኘሮጀክቱ ተግባራዊ የሚሆንበት ወረዳና ዞን፣
3. የኘሮጀክቱ ዋና ዋና ተግባሮች፣
4. የኘሮጀክቱ ጊዜ፣
5. ለኘሮጀክቱ የተመደበው በጀትና
6. ኘሮጀክቱን የሚተገብረውን ድርጅት/አካል

CCRDA

በመግለጽ ከ ሀ እስከ መ የተጠቀሱትን አሟልቶ ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን ጥያቄውን ሲያቀርብ ኮሚሽኑ ማመልከቻውን ተቀብሎ የቀረበለትን ጥያቄ የማስተናገድ ተግባሩን ይቀጥላል፡፡

2.3.3 <u>በመያድ ሥምሪት የክልሉ አመዝኩ ሚና</u>

ሀ. የአማራ ብሔራዊ ክልል አመዝኩ ከመያድ የቀረበውን የኘሮጀክት ኘሮፋይል፣ ተመልክቶ የኘሮጀክት ሃሣቡ ለክልሉ ማኅበረ-ኢኮኖሚያዊ ልማት ኘሮግራም የሚኖረውን አስተዋጽኦ ይመዝናል፡፡

ለ. የቀረበው የመያድ የኘሮጀክት ሃሣብ የህ/ሰቡን ችግር ማዕከል ያደረገ መሆኑንና ተግባራዊ ቢሆን ችግሩን ለማቃለል አዋጭነት ያለው ሆኖ ካገኘው ጥያቄውን ያቀረበው መያድ በዚህ መመሪያ በተቀመጠው የአፈጻጸም አቅጣጫ መሠረት ከሚመለከታቸው የህ/ሰብ ክፍሎች፣ ከሴክተር መ/ቤቶችና ከመስተዳድር አካላት ጋር በመቀናጀት የኘሮጀክት ዝግጅቱን እንዲቀጥል ሊወስን ይችላል፡፡

ሐ. መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ለክልሉ ህ/ሰብ በሚሰጡት አገልግሎት በአንድ አካባቢ እንዳይከማቹ ለማመጣጠን ሲባል የቅድሚያ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገባ አካባቢዎችን ችግር ለማቃለል የክልሉ አመዝ ኩሚሽን ጥያቄ ከቀረበበት አካባቢና መስክ ውጭ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር ጥያቄ ያቀረበው መያድ በሌላ ወረዳ/ዞን እንዲሠማራ፣ ወይም በክልሉ ቅድሚያ በሚሰጣቸው ሌሎች መስኮች እንዲሰማራ መደራደር ይችላል፡፡

መ.የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኩሚሽን ከማንኛውም መያድ ለሚቀርብለት የሥምሪት ጥያቄ የሚሰጠውን ውሣኔ ከ15 ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ጥያቄውን ላቀረበው መያድ እና ለሚመለከታቸው ቢሮዎች በጽሁፍ ይገልፃል፡፡ ለክልሉ መስተዳድር በግልባጭ ያስታውቃል፡፡

ሠ. ኩሚሽኑ በኘሮጀክት ኘሮፋይልና የሥምሪት ወረዳ/ዞን ጥያቄውን ካቀረበው መያድ ጋር የጋራ ስምምነት ላይ ከደረሰ በኘሮጀክት ኘሮፋይሉ መሠረት በሚመለከታቸው የሴክተር መ/ቤቶችና ጥያቄውን ባቀረበው መያድ አማካኝነት ኘሮጀክት በጋራ እንዲዘጋጅ ጉዳዩ ለሚመለከተው ዞን አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኩሚሽን ቅ/ጽ/ቤት የድጋፍ ደብዳቤ ይጽፋል፡፡ ለሚመለከተው የዞን መስተዳድር ጽ/ቤት በግልባጭ ያሳውቃል፡፡

2.3.4 <u>በመያድ ሥምሪትየዞን አመዝ ቅ/ጽ/ቤት ሚና</u>

ሀ. የዞኑ አመዝኩ ቅ/ጽ/ቤትም ከክልሉ አመዝኩ የድጋፍ ደብዳቤ እንደደረሰው ከ10 የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ከዞን መስተዳድርና አግባብ ካላቸው የዞን መመምሪያዎችና ከሚመለከተው መያድ ጋር በሚደረሰው

CGRDA

የጋራ ስምምነት መሠረት ድርጅቱ የሚሰማራበትን ወረዳ በስም ለይቶ ለድርጅቱ በጽሁፍ ያሳውቃል፣

ለ. ለድርጅቱ ደብዳቤው ከደረሰው ከሁለት ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ አግባብ ካላቸው የወረዳ የሴክተር መ/ቤቶችና ከተጠቃሚው ህዝብ ጋር በመሆን የፍላጐት ጥናት በማካሄድ ፕሮጀክት ፕሮፖዛል/ሠነድ/ ቀርጾ እንዲያቀርብ በጽሁፍ ይገለጽለታል ::

ሐ. ድርጅቱ ለሚሠማራበት ወረዳ፣ የወረዳ መስተዳድርና የወረዳ የሴክተር መ/ቤቶች የድጋፍ ደብዳቤ ይጽፋል::

2.3.5 <u>በመያድ ሥምሪት የወረዳ መስተዳድር ሚና</u>

ሀ. የወረዳ መስተዳድር ጽ/ቤት ከዞን አመዝኩ ጽ/ቤት ስለመያድ ሥራ መጀመር የድጋፍ ደብዳቤ እንደደረሰው ከ10 የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የወረዳ መስተዳድርና የሚመለከታቸው የሴክተር መ/ቤቶችና ጥያቄውን ያቀረበው መያድ በጋራ የቀበሌ ቅደም ተከተል በማውጣት ድርጅቱ የሚሠማራባቸውን ቀበሌዎች ይለያሉ፣

ለ. የሚመለከታቸው የወረዳ የሴክተር መ/ቤቶች በፕሮጀክት ዝግጅት የሚሳተፉ ሙያተኞች እንዲመደቡና ከሚመለከተው መያድ ጋር በጋራ እንዲሠሩ ያስተባብራል ፣

ሐ. በፍላጎት ጥናት ለሕዝብ የሚጠቅሙ ፕሮጀክቶችን በሕዝብ ተሳትፎ ለመለየት ለጥናቱ በሚመረጡት ቀበሌዎች፣ የቀበሌመስተዳድሮች የሕዝብ ስብሰባዎችን በመጥራትና የህ/ሰቡን ችግሮች በውል በመለየት የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ ይጽፋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣

መ. በፍላጐት ጥናትና በፕሮጀክት ዝግጅት ወቅት የሚያጋጥሙ አስተዳደራዊ ችግሮችን በመከታተል ይፈታል::

3. <u>የፕሮጀክት ዝግጅት ማጽደቅና ስምምነት ሂደቶች</u> /Process of Project Preparation appraisal and agreement /

የመያድ የፕሮጀክት ዝግጅት ሂደት የሕ/ሰቡን ችግሮች በቅደም ተከተል በመለየት ለችግሮች መፍቻ አስተማማኝ መፍትሄዎችን ለማቀድና ለማደራጀት፡-

ህ/ በፍላጐት ጥናት/ፕሮጀክት መረጣ

ለ/ በፕሮጀክት ሠነድ ዝግጅት

ሐ/ በፕሮጀክት ማጽደቅና

መ/ በፕሮጀክት ስምምነት ሂደቶች ማለፍ ይኖርበታል::

CGRDA

3.1 የኘሮጀክት የፍላጐት ጥናት/የኘሮጀክት መረጣ

የማንኛውም መያድ የልማት ኘሮጀክት መነሻ የሚያደርገው የሕ/ሰቡን ችግሮች በመሆኑ የክልሉን ሕዝብ ያጋጠሙትን የተለያዩ ችግሮች ዋና ዋና ገጽታና መሠረታዊ መንስዔ በውል በማጤን ዘለቄታ ያለው መፍትሄ ለመሻት ሁሉም የልማት አጋሮች (ሕ/ሰቡ፣መያድና የመንግሥት አካላት) የሚሳተፉበት የፍላጐት ጥናት በማካሄድ ችግሮች በቅደም ተከተል ተለይተው ሊታወቁና ችግሮቹን ለማቃለል አቅምን ግምት ውስጥ ያስገባ የኘሮጀክት ምርጫ ሊኖር ይገባል፡፡

የመያድ የፍላጐት ጥናት /ማቁቁቀ በቀቁቱቻበቃበሾሻቻበታቱ/ የሕብረተሰቡን ዋነኛ ችግሮችና ፍላጎቶች ለይቶ ለማወቅ የሚካሄድ በመሆኑ ሕ/ሰቡን ለሚያሳትፍ የማኅበረ- ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ጥናት ተገቢ ትኩረት ይሰጣል፡፡ በመሆኑም በልማት አጋሮች ቅንጅት የሚካሄደው የመያድ የፍላጐት ጥናት፡-

ሀ/ የአካባቢውን ሕ/ሰብ ያጋጠሙትን የችግር ዓይነቶችና ባህሪ በቅደም ተከተል በመለየት ችግሩ ከአካባቢ አካባቢና ከወቅት ወቅት ያለውን ክብደትና ስፋት ማጤን፣

ለ/ ከችግሩ ባህሪ ክብደትና ስፋት አኳያና ከተጠቂው ሕብረተሰብ ሁኔታ የሚመነጩ የሕዝብ ፍላጐቶችን በደረጃ መለየት

ሐ/ በጥናቱ በቅደም ተከተል ከተለዩት ችግሮች መካከል ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገባና ባለ አቅም ሊቃለሉ የሚችሉ ችግሮችንና ፍላጐቶችን በውል ለይቶ ማወቅ የሚያስችል መሆን ይኖርበታል፡፡

የፍላጎት ጥናቱ/ኘሮጀክት መረጣው ሂደት ከሁሉም በላይ የሕ/ሰቡን ችግሮችና መሠረታዊ ፍላጎቶች ማዕከል ያደረገ የመሆኑን ያህል በሂደቱ የሕ/ሰብ ዙሪያ መለስ ተሳትፎ ማረጋገጥ አለበት፡፡

3.2 የኘሮጀክት ሠነድ ዝግጅት

መያድ በአማራ ብሔራዊ ክልል ኘሮጀክት /ኘሮግራም ተግባራዊ ለማድረግ አግባብ ካላቸው የሴክተር መ/ቤቶችና ከኘሮጀክት ተጠቃሚው ህዝብ ጋር የፍላጐት ጥናት/ የኘሮጀክት መረጣ በማካሄድ ኘሮጀክት ቀርፀው የኘሮጀክት ሠነዱን /ኘሮፖዛል/ በየደረጃው ለሚገኙ አግባብ ያላቸው አካላት በማቅረብ ሲጸድቅላቸው የኘሮጀክት ስምምነት ውል ይፈራረማሉ፡፡

3.2.1 የኘሮጀክት ሠነድ ይዘቶች

የኘሮጀክት ሠነድ /ኘሮፖዛል/ የሚከተሉትን ዋና ዋና ነጥቦች ያካተተ ይዘት ሊኖረው ይገባል፣

CCRDA

3.2.1.1 የፊት ሽፋን

የኘሮጀክት ሠነድ የፊት ሽፋን የሚከተሉትን ያካትታል፡፡

ሀ. የኘሮጀክት ስም (ርዕስ) _____

ለ. ኘሮጀክቱን የሚተገብረው ድርጅት _____

ሐ. ኘሮጀክቱ ተግባራዊ የሚሆንበት ወረዳ _____: ዞን _____፣ ክልል _____

መ.ቀንና ዓ.ም. _____

3.2.1.2 የኘሮጀክት ይዘት አጠቃላይ መግለጫ (Excutive summery)

የኘሮጀክት አጠቃላይ መግለጫ Excutive summery የኘሮጀክት ሠነድ አጭር መግለጫ እንደመሆኑ መጠን በሚከተሉት የኘሮጀክት ሠነድ ይዘቶች ላይ ጠቅለል ያለ መረጃ የሚሰጥ መሆን አለበት፡፡

ሀ. ኘሮጀክቱ ተግባራዊ የሚሆንበትን አካባቢ፣

ለ. የኘሮጀክት ተጠቃሚዎችን፣

ሐ. የኘሮጀክቱን ዋና ዋና ተግባሮች፣

መ. ለኘሮጀክቱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን፣ (የሰውኃይል፣ ማቴሪያል፣ ገንዘብ)

ሠ. ከኘሮጀክቱ ፍጻሜ በኋላ የሚጠበቁ ውጤቶች/ለውጥ፣

ረ. የኘሮጀክቱ ጊዜ፣

ሰ. አደረጃጀትና አመራር፣

ሸ. የክትትል ቁጥጥርና ግምገማ ሥልቶች፣

ቀ. የኘሮጀክት ፍጻሜና ርክክብ ሥርዓት፣

3.2.1.3 የኘሮጀክቱ አካባቢ አጠቃላይ ሁኔታና የኘሮጀክቱ አስፈላጊነት/Back Ground and Justification/

ሀ) ኘሮጀክቱ ተግባራዊ የሚሆንበት አካባቢ አጠቃላይ ሁኔታ (Back Ground)

1. ኘሮጀክቱ ተግባራዊ የሚሆንበት አካባቢ ጂኦግራፊያዊ፣ ማኅበራዊ፣ ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊና የፖሊሲ ሁኔታዎች፣
2. ፍላጐት ጥናት/ኘሮጀክት መረጣ ወቅት ሥራ ላይ የዋሉ ዘዴዎች (methodologies) እና አሠራሮች (procedures) ፣
3. በፍላጐት ጥናት/በኘሮጀክት ዕቅድ ዝግጅት ወቅት የህ/ሰቡንና የሚመለከታቸውን የመንግሥት አካላት ተሳትፎ ለማረጋገጥ በሥራ ላይ የዋሉ የአሠራር ዘዴዎች/አግባቦች፣

CCRDA

ለ) <u>የኘሮጀክቱ አስፈላጊነት</u> (Project Justification)

1. የኘሮጀክቱ አጀማመርና አስፈላጊነቱ፣
2. ኘሮጀክቱ ችግሮችን ሊቀርፍ የሚችልባቸው መንገዶች፣

3.2.1.4 የኘሮጀክት ግብ/ዓላማዎች /Project Goals & Objectives/ ፣

3.2.1.5 ኘሮጀክቱ ተግባራዊ የሚሆንበት ስልት/Project Strategy/ ፣

3.2.1.6 ከኘሮጀክቱ ፍጻሜ በኋላ የሚጠበቅ ውጤት/ለውጥ፣

3.2.1.7 በኘሮጀክቱ የሚከናወኑ ዋና ዋና ሥራዎች /Project activities/ ፣

3.2.1.8 ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችና ታሣቢዎች/Risks & assumpations/

3.2.1.9 አደረጃጀትና አመራር/ Organization & Management/

ሀ. ኘሮጀክቱ በማንና በምን አይነት የብቃት ደረጃ እንደሚተገበር፣

ለ. የኘሮጀክት አስተዳደሩ አደረጃጀት፣

ሐ. ለሥራው የሚያስፈልግ የሰው ኃይል፣

መ.የኘሮጀክት አስተዳደሩ ተግባርና ኃላፊነት፣

ሠ. የህ/ሰቡና የሚመለከታቸው ሴክተር መ/ቤቶች ሚናና ኃላፊነቶች መካተት ይገባቸዋል።

3.2.1.10 <u>የኘሮጀክት ወጭ /ግብዓት/ Project cost/inputs/</u>

ለእያንዳንዱ የኘሮጀክት ተግባር በሰው ኃይል፣ በማቴሪያልና በገንዘብ ግብዓት/ ወጭ መልክ የሚያስፈልገው የሐብት ወጭ ስሌት በኘሮጀክት ሠነድ በግልጽ መካተት ይኖርበታል።

ሀ) <u>የሰው ኃይል ቅጥር</u>

1. የኘሮጀክት አፈጻጸም ስኬታማነት በኘሮጀክት አመራር በሚመደበው የሰው ኃይል ሙያ፣ የሥራ ልምድና የሥራ ፍላጐት የሚወሰን በመሆኑ በኘሮጀክት ሠነድ ለኘሮጀክቱ የሚመደቡ ሠራተኞችን ብዛት፣ የሙያ ዓይነትና ደረጃ፣ የሥራ ልምድ፣ ደመወዝና ዜግነት በይፋ መገለጽ አለበት።
2. ለኘሮጀክቱ ሥራ በአገር ቤት ሙያተኛ የማይገኝ ከሆነና የውጭ አገር ሙያተኛ ማስመጣት ግዴታ ከሆነ ወይንም የለጋሽ ድርጅቱ ቅድመ ሁኔታ ሆኖ አስገዳጅ ሲሆን ብቻ የሚፈለገው የውጭ አገር ዜጋ ሙያና የሥራ ልምድ ዝርዝር መረጃ በኘሮጀክት ሠነዱ ተካትቶ መቅረብ አለበት።

ለ) <u>የማቴሪያል አቅርቦት</u>

1. ለኘሮጀክቱ ልዩ ልዩ ተግባራት መቅረብ ያለባቸው ቁሳቁሶችና መሣሪያዎች ግዥ የወጭ ድርሻ ተሰልቶ በኘሮጀክት ሠነድ ተካትቶ መቅረብ ይኖርበታል።

CCRDA

2. ለኘሮጀክቱ አስፈላጊነታቸው የማያጠያይቅ ከውጭ አገር ተገዝተው ከቀረጥ ነፃ የሚገቡና ቀረጥ ተከፍሎባቸው መግባት ያለባቸው ዕቃዎችና መሣሪያዎች ዝርዝርና የወጭ ድርሻ በሠነዱ ውስጥ በግልጽ መካተት አለበት፡፡

ሐ) <u>የገንዘብ /በጀት አመዳደብ</u>

1. አጠቃላይ የኘሮጀክቱን በጀት፣
2. የበጀት ምንጭ /Donor/
3. ለእያንዳንዱ ተግባር የተመደበ በጀት፣
4. አስተዳደራዊ ወጭዎች / Overhead cost/፣
5. የካፒታል /የኘሮጀክት ወጭ ፣ ወዘተ

በወጭ ድልድል ሠንጠረዥ /ቅጽ ተሞልቶ የኘሮጀክት ሠነዱ አካል ሆኖ መቅረብ ይኖርበታል፡፡ (ዝርዝሩን በአባሪው ቅጽ ቁጥር ___ ይመልከቱ)

3.2.1.11 የክትትልና ግምገማ ዘዴዎች፣

3.2.1.12 የሪፖርት ሥልቶች፣

3.2.1.13 የኘሮጀክት ማጠናቀቂያና የርክክብ ሥርዓቶችን/Phase out strategy /

3.3 <u>የኘሮጀክት ማጽደቅ ሂደት /Process of Project appraisal/</u>

- የኘሮጀክት ማጽደቅ ሂደት አንድ ኘሮጀክት ያሳካዋል ተብሎ የታለመለትን ግብ ለማሳካት/ችግር ለማቃለል/ ያለውን ጠቀሜታና በተጠቀሰው የአካባቢ ተጨባጭ ሁኔታ መተግበር የሚችል መሆኑን ለማጣራት የሚከናወን ራሱን የቻለ ተግባር በመሆኑ የወረዳ፣ የዞንና የክልል የሴክተር መ/ቤቶች፣ የመስተዳድር አካላትና መያድ በቅንጅት የተለያዩ ታሣቢዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት በትኩረት ሊያከናውኑት ይገባል፡፡

በማንኛውም የኘሮጀክት ማጽደቅ ሂደት የሚከተሉት መሠረታዊ ጉዳዮች ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

ሀ. የኘሮጀክት ሃሣቡ ከመንግሥት ፖሊሲና የትኩረት ቅደም ተከተሎች ጋር ያለው መጣጣም፣

ለ. የሕ/ሰቡን/የኘሮጀክት ተጠቃሚዎችን/ መሠረታዊ ችግሮች ለመቅረፍ ያለው ብቃት፣

ሐ. የዓላማው ግልጽነት፣

መ. በኘሮጀክት ዝግጅቱ ግምት ውስጥ የገቡ ዋና ዋና ታሣቢዎች ትክክለኛነት፣

ሠ. የቴክኒክ ደረጃ ብቃት፣

ረ. የኘሮጀክት በጀት/ፋይናንስ ድልድሉ ውጤታማነት /cost effectiveness/፣

GCRDA

ሰ. የኘሮጀክት በጀት /Capital Budget/ የሽፋን ድርሻ ከጠቅላላው በጀት ከ70% በታች ያነሰ አለመሆን፣

ሸ. የኘሮጀክቱ ድርጅታዊ መዋቅርና አመራር ኘሮጀክቱን ለመተግበር ያለው ብቃት፣

ቀ. ሕብረተሰባዊ ተቀባይነቱ፣

በ. ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታው፣

ተ. በተፈጥሮ ሐብትና አካባቢ /Environment/ ጥበቃ አሉታዊ ተጽዕኖ የሌለው መሆኑን ወዘተ

3.3.1 በወረዳ ደረጃ የሚከናወን የኘሮጀክት ማጽደቅ ሂደት

ሀ. የህብረተሰብ ተሳትፎን ማዕከል በማድረግ በሚካሄደው የፍላጐት ጥናት ውጤት መሠረት በልማት አጋሮች ቅንጅት /ተጠቃሚ ሴክተር መ/ቤቶችና መያድ /የተዘጋጀው የኘሮጀክት ኘሮፖዛል ሠነድ በሚመለከተው መያድ አማካኝነት ለወረዳ መስተዳድር ጽ/ቤትና ለኘሮጀክት ተጠቃሚ ሴክተሮች የወረዳ ጽ/ቤቶች ለአስተያዬት ይቀርባል።

ለ. የኘሮጀክት ተጠቃሚ የወረዳ ሴክተር መ/ቤቶች ጽ/ቤቶች በኘሮጀክት ኘሮፖዛሉ ሊታረሙ የሚገባቸውንና መካተት ሲገባቸው ያልተካተቱ ጉዳዮችን በመለዬት የኘሮጀክት አስተያዬታቸውን በወረዳው መስተዳድር ሰብሳቢነት በሚጠራው የተጠቃሚ ሴክተር መ/ቤቶችና የሚመለከተው መያድ የጋራ ስብሰባ አቅርበው በሚደረስበት የጋራ ግንዛቤ መሠረት የሚመለከተው መያድ ሠነድን አስተካክሎ ለወረዳው መስተዳድር ጽ/ቤት ያቀርባል።

ሐ. ኘሮጀክቱ በወረዳ የሥልጣን ውክልና የሚፈረም ከሆነ የተስተካከለው የኘሮጀክት ሠነድ ለወረዳው መስተዳድር ጽ/ቤት ከደረሰ ከ10 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የስምምነት ውል እንዲፈረም ለሚመለከታቸው ተፈራራሚ ወገኖች የፊርማውን ዕለት ያሳውቃል።

መ. ኘሮጀክቱ ከወረዳ የሥልጣን ውክልና በላይ ከሆነ ወይም ኘሮጀክቱ በተለያዩ ወረዳዎች የሚተገበር ከሆነ የሚመለከተው መያድ የተስተካከለውን ኘሮጀክት ኘሮፖዛል ሠነድና ኘሮጀክት ኘሮፖዛሉ በወረዳ ደረጃ ተቀባይነት ማግኘቱን የሚገልጽ የወረዳ መስተዳድር የድጋፍ ደብዳቤ ለዞን አመዝኮ ቅ/ጽ/ቤት ያቀርባል።

CCRDA

3.3.2 <u>በዞን ደረጃ የሚከናወን የኘሮጀክት ማጽደቅ ሂደት</u>

ሀ. የዞኑ አመዝኮ ቅ/ጽ/ቤት በወረዳ ደረጃ ታይቶ የቀረበለትን የኘሮጀክት ኘሮፖዛል በ5 ቀናት ጊዜ ውስጥ አግባብ ላላቸው የዞን መምሪያዎች ለአስተያየት ይልካል፡፡

ለ. የዞን መምሪያዎች በቀረበላቸው ኘሮጀክት ኘሮፖዛል ላይ ያላቸውን አስተያየት ኘሮጀክት ኘሮፖዛሉ ከደረሳቸው ከ 10 ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለዞኑ አመዝኮ ቅ/ጽ/ቤት በጽሁፍ ይገልፃል፡፡

ሐ. የዞኑ አመዝኮ ቅ/ጽ/ቤትም ከወረዳና ከዞን መምሪያዎች የደረሱትን አስተያየቶች ካሰባሰበ በኃላ ኘሮጀክት ኘሮፖዛል አቅራቢው መያድ፣ አስተያየት የሰጡ የኘሮጀክት ተጠቃሚ የሴክተር መምሪያዎች ተወካዬች/የመያድ የዴስክ ተጠሪዎች/ በተገኙበት በዞኑ አመዘኮ ቅ/ጽ/ቤት ኃላፊ ሰብሳቢነት በቀረቡት አስተያየቶች ላይ ውይይት ይካሄዳል፡፡

መ.በጋራ ውይይት መስተካከል ያለባቸው ጉዳዮች ከተለዩ በኋላ መስተካከል ያለባቸውን ነጥቦች መንግሥታዊ ያልሆነው ድርጅት አካትቶ የተስተካከለውን የኘሮጀክት ኘሮፖዛል በ10 ቀናት ውስጥ ለዞኑ አመዝኮ ቅ/ጽ/ቤት ያቀርባል፡፡

ሠ. ኘሮጀክት በዞን የሥልጣን ውክልና መፈረም የሚችል ከሆነ፣ ቅ/ጽ/ቤቱ የተስተካከለው ሠነድ እንደደረሰው የሠነዱን ትክክለኛነት አረጋግጦ የኘሮጀክት ስምምነት የሚፈረምበትን ዕለት ለተፈራራሚ መምሪያዎችና መያድ በማሳወቅ ከ10 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የኘሮጀክት ስምምነት እንዲፈረም ያስተባብራል፡፡

ረ. ኘሮጀክቱ ከዞኑ የሥልጣን ውክልና በላይ ከሆነ የሚመለከተው መያድ የተስተካከለውን የኘሮጀክት ኘሮፖዛል ሠነድ ኘሮጀክት ኘሮፖዛሉ በዞኑ ተቀባይነት ማግኘቱን የሚገልጽ የድጋፍ ደብዳቤ ለክልሉ አመዝኮ ይልካል፡፡

3.3.3 <u>በክልል ደረጃ የሚከናወን የኘሮጀክት ማጽደቅ ሂደት</u>

ሀ. የክልሉ አመዝኮ ከዞን የተላከለት የኘሮጀክት ኘሮፖዛል ሠነድ የተሟላ መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ ኘሮጀክት ኘሮፖዛሉ ከደረሰው ከአንድ ሣምንት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ሠነዱን ለሚመለከታቸው ቢሮዎች ለአስተያየት ይልካል፣

CCRDA

ለ. የሚመለከታቸው ቢሮዎችም በቀረበላቸው ኘሮጀክት ኘሮፖዛል ላይ ያላቸውን አስተያየት ከ10 የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለክልሉ አመዝኮ ይልካሉ፣ የኘሮጀክት አስተያየታቸውን በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ የማይልኩ ቢሮዎች ሠነዱን እንዳለ እንደተቀበሉት ይቆጠራል፣

ሐ. የክልሉ አመዝኮም በፊደል ለ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ከየቢሮዎቹ ከሚደርሱት የኘሮጀክት አስተያየቶች ጋር የራሱን አስተያየቶች አካትቶ ከ5 የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ለሚመለከተው መያድ በመላክ ድርጅቱ የተሰጡትን አስተያየቶች አካትቶ የተስተካከለውን የኘሮጀክት ኘሮፖዛል እንዲያቀርብ ያሳውቃል፡፡

መ. የሚመለከተው መያድ ከክልሉ አመዝኮ የኘሮጀክት አስተያየት ከደረሰው ከ15 ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የተላኩለትን አስተያየቶች አካትቶ የተስተካከለውን የኘሮጀክት ሠነድ ለክልሉ አመዝኮ ያቀርባል፡፡

ሠ. የክልሉ አመዝኮም የተስተካከለው ኘሮጀክት ኘሮፖዛል በደረሰው በ3 ቀናት ውስጥ የተስተካከለውን የኘሮጀክት ሠነድ አስተያየት ለሰጡት ቢሮዎች ይልካል፡፡

ረ. ቢሮዎቹ በተስተካከለው የኘሮጀክት ሠነድ ቀደም ሲል የሰጡዋቸው አስተያየቶች መካተት አለመካተታቸውን አረጋግጠው የውል ስምምነት ለመፈፀም ያላቸውን ዝግጁነት የተስተካከለው ሠነድ ከደረሳቸው ከ5 የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለክልሉ አመዝኮ ያሳውቃሉ ፡፡ ተጨማሪ የኘሮጀክት ሠነድ ማስተካከል አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የሚመለከተው ቢሮ፣ አመዝኮና የሚመለከተው መያድ ባሉበት አስፈላጊው ማስተካከል ይደረጋል፣

ሰ. በኘሮጀክት ሠነዱ ላይ ሌላ ማስተካከያ አለመኖሩ ከተረጋገጠ የክልሉ አመዝ ኮሚሽን የኘሮጀክት ስምምነት የሚፈጸምበትን ዕለት ለተፈራራሚ ቢሮዎችና ለሚመለከተው መያድ በማሳወቅ ከ5 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የኘሮጀክት ስምምነት እንዲፈጸም ያስተባብራል፣

3.3.4 <u>በፌዴራል ደረጃ የሚከናወን የኘሮጀክት ማጽደቅ ሂደት</u>፣

መያድ የሚያቀርቧቸው ኘሮጀክቶች በባህሪያቸው ክልላዊ ይዘት የሌላቸው ከሆኑና ከአንድ ክልል ውጭ በተለያዩ ክልሎች የሚፈጸሙ ከሆነ የእነዚህ ኘሮጀክቶች ማጽደቅ ሂደት እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

ሀ. የሚመለከተው መያድ ኘሮጀክት ኘሮፖዛሉን ለፌዴራል አመዘኮ ያቀርባል፣

CCRDA

ለ. የፌዴራል አመዝኮ ከድርጅቱ የቀረበለትን ኘሮጀክት ኘሮፖዛል ድርጅቱ ኘሮጀክቱን ተግባራዊ ለሚያደርግባቸው ክልሎች አመዝ ጽ/ቤት ለአስተያየት ይልካል፣

ሐ. የክልሉ አመዝኮም ኘሮጀክት ኘሮፖዛሉ በደረሰው በ3 ቀን ውስጥ አግባብ ላላቸው የክልል ቢሮዎች የኘሮጀክት ኘሮፖዛሉን ሠነድ ለአስተያየት ይልካል፡፡

መ.አግባብ ያላቸው የክልሉ ቢሮዎችም ኘሮጀክት ኘሮፖዛሉ በደረሳቸው በ10 የሥራ ቀናት ጊዜ ውስጥ ያላቸውን አስተየየት ለክልሉ አመዝኮ ይልካሉ፣

ሠ. የክልሉ አመዝኮም አግባብ ካላቸው ቢሮዎች የደረሱትን አስተያየቶች አሰባስቦ አስተያየቶቹ በደረሱት በ3 ቀናት ውስጥ ለፌዴራል አመዝኮ ይልካል፣

ረ. የፌዴራል አመዝኮም ከክልሉ የተሰጡትን አስተያየቶች አጠቃሎ ለድርጅቱ በመላክ ድርጅቱ እነዚህን አስተያየቶች አካትቶ የተስተካከለ ኘሮጀክት ኘሮፖዛል እንዲያቀርብ ይጠይቃል፡፡

3.4 ኘሮጀክት ስምምነት

ሀ. ማንኛውም ሕጋዊ መያድ የኘሮጀክት ተግባራዊ እንቅስቃሴ ከመጀመሩ በፊት ከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ጋር የኘሮጀክት ስምምነት ውል መፈራረም አለበት፡፡

ለ. ማንኛውም መያድ የኘሮጀክት ውል ሳይፈራረም በራሱ መንገድ በኘሮጀክት መተግበር ተሠማርቶ ከተገኘ የኘሮጀክት ተግባራዊ እንቅስቃሴው እንዲቋረጥ ይደረጋል፡፡

ሐ. የክልሉ አመዝ ኮሚሽን በሚመለከተው መያድ እየተሰጠ ያለውን የህ/ሰብ አገልግሎት ቀጣይነት ለማረጋገጥ ወይም የኘሮጀክት ጊዜያቸው አልፎ ነገር ግን በአፈጻጸም ሂደት ላይ ያሉ የልማት ኘሮጀክቶች እንቅስቃሴ እንዳይቋረጥ ለማገዝ የጊዜ ገደብ በማስቀመጥ ኘሮጀክቶቹን ማስቀጠል ይችላል፡፡

በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ የሚመለከተው መያድ አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት አጠናቆ የኘሮጀክት ስምምነት መፈራረም ይኖርበታል፡፡

መ. የሚመለከተው መያድ ከቁጥጥር ውጭ የሆነ ችግር ያጋጠመው መሆኑ ካልተረጋገጠ በስተቀር በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ስምምነት መፈራረም አለመቻል የኘሮጀክት እንቅስቃሴ መቋረጥን ያስከትላል፡፡

CCRDA

3.4.1 <u>በወረዳ ደረጃ የሚፈጸም የኘሮጀክት ስምምነት</u>

ሀ. የሚፈረመው ኘሮጀክት በጀት ከብር 50,000 (አምሣ ሽህ) በታች ከሆነ የወረዳ መስተዳድሮች የአመዝኩን የማስተባበር ሚና ተከተው የኘሮጀክት ስምምነቱ በወረዳው መስተዳድር፣ በተጠቃሚ ሴክተር መ/ቤቶች የወረዳ ጽ/ቤትና በኘሮጀክቱ ባለቤት መያድ መካከል መፈረም ይችላል።

ለ. የወረዳው መስተዳድር የኘሮጀክት ስምምነት ውል የተፈጸመበትን ሠነድና የጸደቀውን የኘሮጀክት ሠነድ ለተፈራራሚ ሴክተር መ/ቤቶች፣ የወረዳ ጽ/ቤቶችና የዞን መምሪያዎቻቸው፣ ለዞን አመዝኩ ቅ/ጽ/ቤት፣ ለዞን መስተዳድር ጽ/ቤትና ለተፈራራሚው መያድ በመሸኛ ይላካል። ተፈራራሚው መያድ ሥራ እንዲጀምር ያሳውቃል።

ሐ. ተፈራራሚ የወረዳ ሴክተር መ/ቤቶች ጽ/ቤቶችም በስምምነቱ የተካተቱትን ኃላፊነቶቻቸውን ለመወጣትና ጎብረተሰቡን የልማት ተጠቃሚ ለማድረግ ለኘሮጀክቱ ተግባራዊነት አስፈላጊውን የሙያ ድጋፍ ለመስጠት በድርጊት መርሃ ግብር ዝግጅትም ሆነ በተግባራዊ አፈጻጸም የሚኖራቸውን ሚና አቅደው ለፈጻሚ ሙያተኞች ግልጽ ያደርጋሉ።

3.4.2 <u>በዞን ደረጃ የሚፈጸም የኘሮጀክት ስምምነት</u>

ሀ. የኘሮጀክት በጀታቸው ከወረዳ የመፈራረም የሥልጣን ውክልና በላይ የሆኑና እስከ ብር 500,000 (አምስት መቶ ሽህ) በጀት ያላቸው ኘሮጀክቶች በዞን ደረጃ ይፈረማሉ።

ለ. የዞን አመዝ ቅ/ጽ/ቤት ከሚመለከተው መያድ በዞን ደረጃ የጸደቀው የኘሮጀክት ሠነድ ከለጋሽ ድርጅት የበጀት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ጋር ተያይዞ ሲቀርብለት ከተፈራራሚ ወገኖች ጋር በመወያየት ከ10 የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የኘሮጀክት ስምምነት ውል የሚፈጸምበትን ዕለት ወስኖ በማሳወቅና የስምምነት ሠነድ በማዘጋጀት በዞን አመዝኩ ቅ/ጽ/ቤት፣ በኘሮጀክት ተጠቃሚ የዞን ሴክተር መ/ቤቶች፣ መምሪያዎችና በኘሮጀክት ፈጻሚ መያድ መካከል የኘሮጀክት ስምምነት ውል ይፈረማል።

ሐ. የኘሮጀክቱ የበጀት ጣሪያ በወረዳ ደረጃ ስምምነት የሚፈረም ሆኖ እያለ ነገር ግን ኘሮጀክቱ በባህሪው ከአንድ ወረዳ ውጭ በተለያዩ ወረዳዎች የሚተገበር ከሆነ ለአፈጻጸም አመችነቱ ሚዛን ተሰጥቶት የሚመለከታቸውን ወረዳዎች የኘሮጀክት ስምምነት ሃላፊ በማካተት ስምምነቱ በዞን ደረጃ ይፈረማል።

CCRDA

መ.የዞን አመዝ ቅ/ጽ/ቤት የተፈረመውን የኘሮጀክት ስምምነት የውል ሠነድና የጸደቀውን የኘሮጀክት ሠነድ በመሸኛ ለዞን መስተዳድር ጽ/ቤት፣ ለተፈራራሚ የሴክተር መ/ቤቶች የዞን መምሪያዎች ፣ ለክልሉ አመዝ ኮሚሽን፣ ለተፈራራሚው መያድና ኘሮጀክቱ ተግባራዊ ለሚሆንበት ወረዳ ጽ/ቤት በመሸኛ ይልካል። ድርጅቱ ሥራ እንዲጀምር ያሳውቃል።

ሠ. ተፈራራሚ የዞን ሴክተር መ/ቤቶች መምሪያዎች ለወረዳ የሴክተር ጽ/ቤቶቻቸው የጸደቀውን የኘሮጀክት ሠነድና የኘሮጀክት ስምምነት ውል ኮፒዎች በመላክ ለኘሮጀክት አፈጻጸሙ ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ቀጣይነት ያለው ድጋፍ ይሰጣሉ።

ረ. የዞን አመዝኮ ቅ/ጽ/ቤት ከወረዳ መስተዳድር የሚላክለትን በወረዳ ደረጃ የተፈረመ ኘሮጀክት የውል ስምምነትና የኘሮጀክት ሠነድ ፎቶ ኮፒዎች በመሸኛ ለዞን መስተዳድር ጽ/ቤትና ለክልሉ አመዝኮ ይልካል።

3.4.3 <u>በክልል ደረጃ የሚፈጸም የኘሮጀክት ስምምነት</u>

ሀ. የኘሮጀክት በጀታቸው ለዞን ከተሰጠው የሥልጣን ውክልና ከብር 500,000.00(አምስት መቶ ሽህ) በላይ የሆኑ ኘሮጀክቶች የኘሮጀክቶች የውል ስምምነት በክልሉ አመዝ ኮሚሽን፣ በተጠቃሚ የሴክተር መ/ቤቶች ቢሮዎችና በሚመለከተው መያድ መካከል በክልል ደረጃ ይፈረማል።

ለ. ኘሮጀክቱ በዞን የሥልጣን ውክልና መፈረም የሚችል ሆኖ እያለ ነገር ግን ኘሮጀክቱ ከአንድ ዞን በላይ በተለያዩ ዞኖች ተግባራዊ የሚሆን ከሆነ የሚመለከታቸውን ዞኖች የኘሮጀክት አስተያዬት በማካተት የኘሮጀክት ስምምነቱ በክልሉ አመዝ ኮሚሽን በተጠቃሚ ሴክተር ቢሮዎችና በኘሮጀክቱ ፈጻሚ መያድ መካከል በክልል ደረጃ ይፈረማል።

ሐ. የክልሉ አመዝኮ የቢሮዎችን የኘሮጀክት አስተያየት ያካተተ የተስተካከለ ሠነድ የለጋሽ ድርጅት የበጀት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንደደረሰው በ10 የሥራ ቀናት ውስጥ የስምምነት ሰነድ ያዘጋጃል። ከተፈራራሚዎች ጋር በመነጋገር የኘሮጀክት ስምምነት ፊርማ የሚካሄድበትን አመቺ ዕለት በመወሰን የኘሮጀክት የውል ስምምነት ፊርማ እንዲፈፀም ያደርጋል።

መ.የክልሉ አመዝኮ ስምምነት የተፈፀመበትን ሰነድና የጸደቀውን ኘሮጀክት ኘሮፖዛል ኮፒ ለድርጅቱ በመላክ ድርጅቱ ስራ እንዲጀምር በጽሁፍ ያሳውቃል፣ የኘሮጀክት ስምምነት ሰነዱንና የጸደቀውን የኘሮጀክት ሠነድ

CCRDA

ለተፈራራሚ ቢሮዎች፣ ለዞን መስተዳድር ጽ/ቤትና ለዞን አመዝኪ ቅ/ጽ/ቤት እንዲሁም ለፌዴራል አመዝኪ ይልካል።

ሠ. ተፈራራሚ ቢሮዎችም የስምምነት ሰነዱንና የጸደቀውን የኘሮጀክት ሠነድ በተዋረድ ላሉት የዞን መምሪያዎችና የወረዳ ጽ/ቤቶቻቸው /Lower functionaries/ ይልካሉ።

ረ. የክልሉ አመዝ ኮሚሽን ከዞን አመዝ ቅ/ጽ/ቤት የሚላክለትን በዞን ደረጃ የጸደቀውን የኘሮጀክት ሠነድና የኘሮጀክት የውል ስምምነት ፎቶ ኮፒ በመሸኛ ለአብክመ ም/ቤትና ለኢፌዲሪ አመዝኪ ይልካል።

3.4.4 <u>በፌዴራል ደረጃ የሚፈጸም የኘሮጀክት ስምምነት</u>

ሀ. የኘሮጀክቶች ባህሪ ክልል ተኮር ይዘት የሌለው ከሆነና ከአንድ ክልል በላይ በተለያዩ ክልሎች የሚተገበሩ ከሆነ የሚመለከታቸውን ክልሎች የኘሮጀክት አስተያዬት በማካተት የኘሮጀክት ስምምነቱ በፌዴራል ደረጃ ይፈረማል።

ለ. በመያድ የቀረበው ኘሮጀክት ኘሮፖዛል በፌዴራል አመዝኪ ተቀባይነት አግኝቶ የበጀት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሲቀርብ የኘሮጀክት የውል ስምምነት በፌዴራል ደረጃ ይፈፀማል፣

ሐ. የፌዴራል አመዝኪ ስምምነት የተፈፀመበትን ሰነድና የተስተካከለውን ኘሮጀክት ኘሮፖዛል ኮፒ ስምምነት ከተፈፀመ በ10 ቀናት ጊዜ ውስጥ ለሚመለከተው ክልል አመዝኪ ይልካል፣

መ. የክልሉ አመዘኮም የቀረበለትን የስምምነት ሰነድና የተስተካከለውን ኘሮጀክት ዶክሜንት በ5 ቀናት ውስጥ አግባብ ላላቸው ቢሮዎችና ለዞን አመዝኪ ቅ/ጽ/ቤቶች ይልካል፣

ሠ. አግባብ ያላቸው ቢሮዎችም ከአመዝኪ የደረሳቸውን የስምምነት ሰነድና ኘሮጀክት ዶክሜንት ኮፒ ዶክሜንቶቹ በደረሱዋቸው በ5 ቀናት ውስጥ በተዋረድ ለሚገኙ መምሪያዎችና ጽ/ቤቶች ይልካሉ።

3.4.5 <u>የኘሮጀክት ስምምነት ሠነድ ይዘት</u> / <u>Contents of Project Agreement Document</u>/

የኘሮጀክት ስምምነት ሠነድ የሚከተሉትን ነጥቦች ሊያካትት ይገባል፣

ሀ. የተፈራራሚ መ/ቤቶች ስም፣

ለ. ስምምነት የሚፈፀምበት ኘሮጀክት ስም፣

ሐ. ኘሮጀክቱ የሚተገበርበት ዞንና ወረዳ፣

መ.ዋና ዋና የኘሮጀክት ኮምፖነንቶች/ስራዎች

ሠ. የአመዝኪ/የወረዳ መስተዳድር ኃላፊነቶችና ግዴታዎች፣

CCRDA

ረ. የአስፈጻሚ መ/ቤቶች /LB's/ ኃላፊነቶችና ግዴታዎች

ሰ. የፈጻሚው ድርጅት ኃላፊነቶችና ግዴታዎች

ሸ. የኘሮጀክቱ አጠቃላይ በጀት

ቀ. የኘሮጀክት ዘመን /Duration/

በ. የኘሮጀክት ተጠቃሚዎች ብዛት

ተ. የኘሮጀክት ተፈራራሚ መ/ቤት ወይም መያድ ስም፣ኘሮጀክቱን የፈረመው/ችው ኃላፊ ስምና ፊርማ፣ ስምምነቱ የተፈፀመበት ቀንና ዓ.ም፣ የተፈራራሚው መ/ቤት ወይም መያድ ክብ ማህተም፣

4. <u>የመያድ ኘሮጀክት አፈጻጸም ሂደት /Process of NGOs project implementation/</u>

4.1 <u>የኘሮጀክት ስምምነት ማክበር</u> /Conformity to the project agreement/

ሀ. መያድ በፈጸሙት የኘሮጀክት ስምምነት ውል መሠረት ኘሮጀክቶችን የመተግበር ግዴታ አለባቸው።

ለ. ማንኛውም በአማራ ብሔራዊ ክልል ለመጀመሪያ ጊዜ ሥራ የሚጀምር አዲስ ኘሮጀክት ተፈራራሚ መያድ ኘሮጀክት ከተፈራረመ ከ3 ወራት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ አስፈላጊውን የገንዘብ፣ የማቴሪያልና የሰው ኃይል በማንቀሳቀስ የኘሮጀክቱን ተግባራዊ እንቅስቃሴ መጀመር አለበት።

ሐ. በአማራ ብሔራዊ ክልል በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኝ ማንኛውም ነባር መያድ አዲስ የኘሮጀክት ስምምነት ውል ከተፈራረመ የኘሮጀክቱ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ከአንድ ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ መጀመር አለበት።

መ. ተፈራራሚ መያድ ከላይ በተጠቀሱት ጊዜያት ውስጥ ሥራ መጀመር የማያስችላቸው አጥጋቢ ምክንያት መኖሩ ለክልሉ አመዝ ኮሚሽን ቀርቦ ሲታመንበት እንደሁኔታው ከ3 ወራት ያልበለጠ ተጨማሪ የኘሮጀክት ቅድመ ዝግጅት ጊዜ ሊሰጣቸው ይችላል።

ሠ. በማንኛውም ሁኔታ የኘሮጀክት ተግባራዊ እንቅስቃሴ ሳይጀመር ከ10 ወር በላይ ከዘገየ የኘሮጀክት ስምምነቱ ውል እንደተቋረጠ ይቆጠራል።

ረ. መያድ የኘሮጀክት ተፈራራሚ ወገኖችና ተጠቀሚው ህብረተሰብ ሳያውቁት የኘሮጀክት ተግባራትንም (physical work) ሆነ የበጀት ድልድል ለውጥ ማድረግ አይችሉም።

CCRDA

ሰ. ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ካላጋጠመ በስተቀር የመያድ ኘሮጀክቶች ተግባራዊነት መቋረጥ የለበትም፡፡ በኘሮጀክት ተግባራዊ አፈጻጸም ሂደት የኘሮጀክት ተግባራዊነት የሚያደናቅፍ ችግር ካጋጠመ መያድ ለሚመለከታቸው የወረዳ መስተዳድሮች፣ የዞንና የክልል አመዝኩ ጽ/ቤቶች ሪፖርት በማድረግ ችግሩ የሚቃለልበትን መንገድ መፈለግ አለባቸው፡፡

ሸ. ከተፈራራሚ መንግሥታዊ አካላት በስተቀር ሌሎች የመንግሥት አካላት በመያድ የሥራ እንቅስቃሴ ጣልቃ መግባት አይችሉም፡፡ በመያድ ኘሮጀክቶች አፈጻጸም ችግር መኖሩን ከተገነዘቡ ለሚመለከታቸው የወረዳ መስተዳድሮች ወይም ለአመዝኩ ጽ/ቤቶች በጊዜው በማመልከት ወቅታዊ እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ ይችላሉ፡፡

ቀ. ተፈራራሚ/ተጠቃሚ የሴክተር መ/ቤቶች የኘሮጀክቱን ተግባራዊ አፈጻጸም ስኬታማ ለማድረግ ከእነርሱ የሚጠበቀውን ሙያዊና ቁሣዊ ድጋፍ ይሰጣሉ፡፡ በመስክ ጉብኝት፣ በሪፖርትና በጋራ የግምገማ መድረኮች ተገቢ የክትትልና ቁጥጥር ተልዕኮአቸውን ይወጣሉ፡፡ አፈጻጸሙን አስመልክቶ ለሚመለከታቸው የበላይ አካላት ሪፖርት ያቀርባሉ፡፡

በ. የመያድ ኘሮጀክት ሴክተር ተኮር ዋና ዋና ተግባሮች አፈጻጸም የሚመለከተውን የኘሮጀክት ተፈራራሚ/ተጠቃሚ የሴክተር መ/ቤት አስተዋጽኦ ያካተተ፣ ተፈላጊውን የጥራት ደረጃ የጠበቀና የጋራ አቅምን የሚገነባ ሂደት እንዲኖረው ከሴክተር መ/ቤቶች ጋር ለሚኖረው ቅንጅት ተገቢ ትኩረት መስጠት አለበት፡፡

ተ. መያድ ከኘሮጀክት ተፈራራሚ /ተጠቃሚ የሴክተር መ/ቤቶችና ከተጠቃሚው ህ/ሰብ ጋር በመስክ ጉብኝት፣ በሪፖርትና በጋራ ግምገማ መድረኮች ለሚያካሂዱት የኘሮጀክት ክትትልና ቁጥጥር አመች የሆነና ግልጽነት ያለው አሠራር መከተል አለባቸው፡፡

4.2 <u>የኘሮጀክት ዓመታዊ የድርጊት መርሃ ግብር /action plan/</u>

ሀ. የመያድ ኘሮጀክት ተግባራዊ አፈጻጸም በድርጊት መርሃ ግብር /action plan/ መመራት አለበት፡፡

ለ. በማንኛውም ደረጃ ተፈርሞ በወረዳ ባለቤትነት ተግባራዊ የሚሆን አዲስ ኘሮጀክት ተግባራዊ እንቅስቃሴ ከመጀመሩ በፊት በወረዳ የልማት አጋሮች

CCRDA

ቅንጅት የድርጊት መርሃ ግብር ተዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው የኘሮጀክት ተፈራራሚ /ተጠቃሚ መ/ቤቶች ቀርቦ መጽደቅ አለበት፡፡

ሐ. በሂደት ላይ ያሉ ኘሮጀክቶች ዓመታዊ የድርጊት መርሃ ግብር በልማት አጋሮች ቅንጅት ተዘጋጅቶ አዲስ የበጀት ዓመት ከመጀመሩ አንድ ወር(ህዳር 30) በፊት ለኘሮጀክት ተፈራራሚ ወገኖች ቀርቦ መጽደቅ አለበት፡፡

መ. ዓመታዊ የድርጊት መርሃ ግብር በድርጊት መርሃ ግብር ማቅረቢያ ቅጽ ተሞልቶ መቅረብ አለበት፡፡ አባሪ ቁጥር ___ ይመልከቱ፡፡

ሠ. የኘሮጀክት ተፈራራሚ ወገኖች የድርጊት መርሃ ግብሩ እንደደረሳቸው ከ15 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ አስተያዬት ሰጥተው ከሚመለከታቸው ወገኖች ጋር የጋራ ግንዛቤ ላይ ለመድረስ ጥረት ካላደረጉ የቀረበውን የድርጊት መርሃ ግብር እንደተቀበሉት ተቆጥሮ ይጸድቃል፡፡

ረ. የመያድ የድርጊት መርሃ ግብር እስከ ህዳር 30 ካልቀረበ የክልሉ አመዝኪ የድርጊት መርሃ ግብር እስከ ታህሳስ 10 እንዲቀርብ በጽሁፍ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

ሰ. የአብክመ አመዝኪ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው የሚመለከታቸው የመያድ የበላይ ኃላፊዎች በአካል ቀርበው ለምን የድርጊት መርሃ ግብሩን በጊዜው ማቅረብ እንዳልተቻለ እንዲያስረዱ ሊጠይቅና እንዳስፈላጊነቱ እርምጃ ሊወስድ ይችላል፡፡

ሸ. የኘሮጀክት የድርጊት መርሃ ግብር በወረዳ/በዞን የልማት አጋሮች ቅንጅት ተዘጋጅቶ የኘሮጀክት ተጠቃሚ የሴክተር መ/ቤቶችን አስተያዬት አካትቶ በኘሮጀክት ተፈራራሚዎች ይጸድቃል፡፡ የፀደቀው የድርጊት መርሃ ግብር ለተፈራራሚ ወገኖችና በየደረጃው ላሉት የኘሮጀክት ተጠቃሚ የሴክተር መ/ቤቶችና የመስተዳድር አካላት የድርጊት መርሃ ግብሩ ከፀደቀ ከአምስት ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ይላካል፡፡

4.3 <u>በኘሮጀክት አፈጻጸም የህዝብ ተሳትፎን ማረጋገጥ</u>

ማንኛውም ሕዝብን ተጠቃሚ የሚያደርግ የልማት ሥራ ያለ ህብረተሰቡ ተሳትፎ ዘለቄታ ሊኖረው ስለማይችል መያድ ለሕዝቡ በሚሰጡት አገልግሎት ከፍላጐት ጥናት እስከ ኘሮጀክት ፍጻሜ በሚኖረው የአፈጻጸም ሂደት ለህ/ሰብ ተሳትፎ መረጋገጥ ተገቢ ትኩረት መሰጠት ይኖርባቸዋል፡፡

CCRDA

በመያድ ፕሮጀክቶች የሕ/ሰቡ ዙሪያ መለስ ተሳትፎ መረጋገጥ፡-

ሀ/ ሕ/ሰቡ የትኩረት ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ፍላጐቶች/ችግሮች በሚገባ መለዬት ያስችላል፣

ለ/ የአካባቢውን ሕ/ሰብ ዕውቀቶች /Indigenous knowledge / በመጠቀም ችግር መፍታት ለቀጣይነቱ ዋስትና ይሰጣል፣

ሐ/ የውሣኔ አሰጣጥ ሂደትን ያቀላጥፋል፣

መ/ የሕ/ሰቡን ተሳትፎ በማሳደግ የፕሮጀክት ወጭን ይቀንሳል፣

ሠ/ በመያድ ፕሮጀክቶች ላይ የሕ/ሰቡን የባለቤትነት ስሜት ይፈጥራል፡፡

ረ/ የልማቱን ቀጣይነት ዋስትና ይሰጣል፡፡

ሰ/ የሕ/ሰቡን በራስ መተማመንና የመወሰን አቅም ያጐለብታል፡፡

በመሆኑም መያድ በማንኛውም የፕሮጀክት ተግባራዊ አፈጻጸም ሂደት የህ/ሰቡን ፍላጐትና የሁሉንም ጸታዎች ተሳትፎ በተግባር ማረጋገጥ አለባቸው፡፡ በፕሮጀክት አፈጻጸም የህ/ሰብ ተሳትፎን እውን ለማድረግ በዋነኛነት በቀበሌና ከቀበሌ በታች ያሉትን የሕዝብ አስተዳደርና የልማት አደረጃጀቶች የፕሮጀክቱ ልዩ ባህሪ ከሚጠይቀው የተጠቃሚዎች አደረጃጀት ጋር በማጣመር የሕብረተሰቡን አቅም በሚያጐለብት መንገድ ለመጠቀም ተገቢ ትኩረት መስጠት አለባቸው፡፡

4.4 <u>የፕሮጀክት ሐብት አጠቃቀምና አስተዳደር</u>

ሀ. የፕሮጀክቱ ማንኛውም ሐብት የፕሮጀክቱንዓላማ ከግብ ማድረስ ለሚያስችሉ የፕሮጀክት ተግባሮች ማከናወኛ ብቻ ሥራ ላይ ይውላል፡፡

ለ. ከፕሮጀክት ተፈራራሚዎች የጋራ ዕውቀት ውጭ የአንድን ፕሮጀክት በጀት /ሐብት ወደሌላ ፕሮጀክት አዛውሮ መጠቀም አይቻልም፡፡

ሐ. በክልሉ ውስጥ በሚገኙ የተለያዩ ፕሮጀክቶች መካከል የሚደረግ የተሽከርካሪና ሌሎች ንብረቶች መዋዋስ በፕሮጀክት አፈጻጸም ሂደት ላይ የሚያስከትለው ጉዳት እስከሌለ ድረስ ከሁለት ወር ላልበለጠ ጊዜ ተግባራዊ መሆን ይችላል፡፡

መ.ከሁለት ወር በላይ የሚደረግ የፕሮጀክት ንብረት መዋዋስ በቅድሚያ የዞን አመዝ ቅ/ጽ/ቤትን ወይም የክልል አመዝኩን ድጋፍ ማግኘት አለበት፡፡

ሠ. ከአንድ ክልል በላይ ሽፋን ያላቸው ፕሮጀክቶች የንብረት መዋዋስ በቅድሚያ የአማራ ክልል አመዝ ኮሚሽንንና የፌዴራል አመዝኩን ድጋፍ ማግኘት አለበት፡፡

CCRDA

ረ. ኘሮጀክቱን ተግባራዊ የሚያደርገው መያድ የኘሮጀክቱ የሥራ ጊዜ ከመጠናቀቁ 6 ወር በፊት በቀሪው የኘሮጀክት የሥራ ጊዜ ሥራ ላይ የማያውለውን የኘሮጀክት በጀት \Fund/ መጠን ለተፈራራሚ ወገኖች ማሳወቅ አለበት፡፡

ሰ. በሥራ ላይ የማይውል የበጀት \Fund/ መጠን ሪፖርት እንደደረሰ በ15 ቀናት ውስጥ የዞን ወይም የክልል ተፈራራሚዎች የሚመለከተው መያድ በቀሪው የኘሮጀክት ጊዜ በጀቱን እንዴት መጠቀም እንደሚችል ይወስናሉ፡፡

ሸ. በጀቱን በኘሮጀክቱ ላልተካተቱ ሌሎች ተግባራት ለመጠቀም ውሣኔ ላይ ከተደረሰ በጀቱ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት በበጀት አጠቃቀሙ ላይ የለጋሽ ድርጅት /Donor/ ስምምነት አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የለጋሽ ድርጅቱ ድጋፍ በቅድሚያ ይጠየቃል፡፡

4.5 <u>የኘሮጀክት ሠነድ /Project Document/ ማስተካከል</u>

ሀ. ኘሮጀክት በመተግበር ሂደት ላይ እያለ በኘሮጀክት ዝግጅትና ስምምነት ሂደት በውል ያልታዩ ችግሮች ካጋጠሙ ሐብትን በአግባቡ ለመጠቀም የኘሮጀክቱ ዓላማ ሳይቀየር የኘሮጀክት ሠነድ /Project Document/ ሊስተካከል ይችላል፡፡

ለ. የኘሮጀክት ማስተካከያ ጥያቄው ከኘሮጀክት ተጠቃሚው ህ/ሰብ፣ ኘሮጀክቱን ከሚተገብረው መያድ ወይም ከሌሎች የኘሮጀክት ተፈራራሚ/ተጠቃሚ የሴክተር መ/ቤቶች ሲቀርብ ወይም በሁሉም ወገኖች የጋራ ግምገማ የተለዩ የኘሮጀክት ሠነድ ማስተካከል የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ሲያጋጥሙ በሁሉም የኘሮጀክት ተፈራራሚ ወገኖች ተሳትፎ የኘሮጀክት ሠነድ ሊስተከከል ይችላል፡፡

ሐ. ከማንኛውም ወገን የኘሮጀክት ተፈራራሚ ወገኖችን ለሚያስተባብረው የዞን አመዝ ቅ/ጽ/ቤት ወይም ለክልሉ አመዝኩ የኘሮጀክት ማስተካከያ የሚያስፈልገው የኘሮጀክት ክፍልና አማራጭ መፍትሄዎች የያዘ ጥያቄ በጽሁፍ ሲቀርብ በ15 የሥራ ቀናት ጊዜ ውስጥ ለኘሮጀክት ተፈራራሚ ወገኖች የጋራ ስብሰባ ይቀርባል፡፡

መ. የቀረበው የኘሮጀክት ማስተካከያ ሃሣብ በኘሮጀክት ተፈራራሚ ወገኖች ተቀባይነት አግኝቶ የኘሮጀክት ሠነዱን ለመቀየር ወይም ለማሻሻል ስምምነት ላይ ከተደረሰ በኘሮጀክት ሠነድ ላይ እንደሚከሰተው ለውጥ ባህሪ የኘሮጀክት ስምምነቱ በጠቅላላ ሊቀየር ወይም የኘሮጀክት መግባቢያ ሠነድ / memorandum of understanding / ሊፈረም ይችላል፡፡

ሠ. የኘሮጀክት ተፈራራሚ ወገኖች የቀረበውን የኘሮጀክት ማሰተካከያ ሃሣብ ካልተቀበሉት ኘሮጀክቱ በድሮው ይዘቱ ተግባራዊነቱ ይቀጥላል፡፡

CCRDA

ረ. የኘሮጀክት ማስተካከያው መግባቢያ ሠነድ / memorandum of understanding / ዋናውን የኘሮጀክት ስምምነት ሠነድ በፈረሙት ተፈራራሚ ወገኖች መፈረምና የመጀመሪያው ሠነድ ለተላከላቸው ወገኖች ሁሉ መሠራጨት ይኖርበታል።

4.6 የኘሮጀክት ጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄ

ሀ) መያድ ለሚተገብሯቸው ኘሮጀክቶች የኘሮጀክት ጊዜ ማራዘም /project extension/ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኙት የኘሮጀክት ጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄያቸውን እያንዳንዱ ኘሮጀክት ከመጠናቀቁ ከሶስት ወር በፊት ኘሮጀክቱን ለተፈራረሙት የፌዴራል፣ የክልል ወይም የዞን አመዝኩ ጽ/ቤቶች ማቅረብ ይኖርባቸዋል።

ለ) በየደረጃው ያሉት ተፈራራሚ የአመዝኩ ጽ/ቤቶችም የመያድ የኘሮጀክት ማጠናቀቂያ /terminal evaluation report/ ሪፖርት ተዘጋጅቶ የቀረበ መሆኑን ያረጋግጣሉ።

ሐ) በፌዴራል ደረጃ የተፈረመ ኘሮጀክት የጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄ ሲቀርብ አግባብ ካላቸው የማዕከል ተፈራራሚ አካላት፣ የክልል አመዝ ኮሚሽንና የኘሮጀክት ተጠቃሚ ቢሮዎች፣ የዞን አመዝኩ ቅ/ጽ/ቤት፣ የዞን የኘሮጀክት ተጠቃሚ መምሪያዎችና የሚመለከተው መያድ የሚካፈሉበት ቡድን በማቋቋም የወረዳ መስተዳድር፣ የኘሮጀክት ተጠቃሚ የሴክተር መ/ቤቶችና የኘሮጀክት ተጠቃሚ ሕዝብ ተወካዮች በተገኙበት ግምገማ ይካሄዳል።

መ) በክልል ደረጃ የተፈረመ ኘሮጀክት የጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄ ለክልል አመዝኩ ሲቀርብ ከኘሮጀክት ተፈራራሚ ቢሮዎች/ኮሚሽን፣ ከዞን አመዝኩ ቅ/ጽ/ቤትና ከኘሮጀክት ተጠቃሚ የዞን የሴክተር መ/ቤቶች መምሪያዎች በተውጣጣ ቡድን አማካኝነት የኘሮጀክት ተጠቃሚ ወረዳ መስተዳድር አካላት፣ የወረዳ የሴክተር መ/ቤቶች የጽ/ቤት ተወካዮችና የኘሮጀክት ተጠቃሚዎች በሚገኙበት የኘሮጀክት የመስክ ግምገማ ይካሄዳል።

ሠ) በዞን ደረጃ የተፈረመ ኘሮጀክት የጊዜ የማራዘሚያ ጥያቄ ለዞን አመዝኩ ቅ/ጽ/ቤት ሲቀርብ ከዞን አመዝ ቅ/ጽ/ቤት፣ ከኘሮጀክት ተፈራራሚ የዞን መምሪያዎች፣ ከኘሮጀክት ተጠቃሚ ወረዳ መስተዳድር፣ ከወረዳ የሴክተር መ/ቤቶች ጽ/ቤቶችና ከሚመለከተው መያድ በተውጣጣ የኘሮጀክት ግምገማ ቡድን የኘሮጀክት የተጠቃሚው ህብረተሰብ ተወካዮችና የቀበሌ መስተዳድሮች በተገኙበት የመስክ ግምገማ ይካሄዳል።

ረ) የፌዴራል የግምገማ ቡድን የግምገማ ሪፖርቱን ለፌዴራል አመዝኩ ያቀርባል። የፌዴራሉ አመዝኩም የግምገማ ሪፖርቱን ለሚመለከተው መያድ ፣ አግባብ ላላቸው ሌሎች ተፈራራሚ አካላትና ለክልል አመዝ ኮሚሽን ይልካል።

CCRDA

ሰ. የክልል የግምገማ ቡድን የግምገማ ሪፖርቱን ለክልሉ አመዝኮ ያቀርባል፡፡ የክልሉ አመዝኮም የግምገማ ሪፖርቱን ለሚመለከተው መያድ ፣ አግባብ ላላቸው የክልል ቢሮዎች፣ የዞን አመዝ ቅ/ጽ/ቤቶችና የዞን መስተዳድር ጽ/ቤቶችና ለፌዴራል አመዝኮ ይልካል፡፡

ሸ. የዞን የግምገማ ቡድን ሪፖርቱን ለዞን አመዝኮ ቅ/ጽ/ቤት ያቀርባል፡፡ የዞኑ አመዝኮ ቅ/ጽ/ቤትም የግምገማ ሪፖርቱን ለሚመለከተው መያድ፣ ለክልሉ አመዝኮና ለተፈራራሚ የዞን መምሪያዎች፣ ለወረዳ መስተዳድርና ለወረዳ የሴክተር መ/ቤቶች ጽ/ቤቶች ይልካል፡፡ ተፈራራሚ የዞን መምሪያዎችም ከዞኑ አመዝኮ የደረሳቸውን የግምገማ ሪፖርት ለክልል ቢሮዎቻቸው ይልካሉ፡፡

ቀ. የተጠናቀቀው ኘሮጀክት ሲገመገም የኘሮጀክት አፈጻጸሙ አጥጋቢ ውጤት ማሳየቱ ከተረጋገጠና በአፈጻጸም ሂደት ድርጅቱ ከህብረተሰቡና ከሚመለከታቸው የሴክተር መ/ቤቶች ጋር በቅንጅት የሠራ መሆኑ ከተረጋገጠ የኘሮጀክት ጊዜ ማራዘሚያ ወይም ማስፋፊያ ጥያቄው ተቀባይነት ያገኛል፡፡

በ. የኘሮጀክት ማጠቃለያ ሪፖርትና የኘሮጀክት መገምገሚያ ነጥቦች በአባሪ ቅጽ ___ ቀርቧል፡፡

5. <u>የመያድ ኘሮጀክት ክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት</u>

ክትትልና ቁጥጥር በኘሮጀክት አፈጻጸም ሂደት በየጊዜው የሚነሱ መሠረታዊ ጉዳዮችን መከታተያ አይነተኛ የአመራር መሣሪያ ነው፡፡ ክትትልና ቁጥጥር በአመራር መሣሪያነቱ የኘሮጀክት የፊዚካል ሥራ አፈጻጸምና የበጀት አጠቃቀም በድርጊት መርሃ ግብሩ በታቀደው መሠረት ተግባራዊ መሆኑን ኘሮጀክቱ በተቀመጠለት የአፈጻጸም አቅጣጫ /implementation strategy/ መሠረት ተግባራዊ መደረጉንና የሚመለከታቸው የልማት አጋሮችና የኘሮጀክት ተጠቃሚዎች /stakeholders/ ተሳትፎ በኘሮጀክት አፈጻጸም ሂደት መረጋገጡን ማወቅ ያስችላል፡፡ ክትትልና ቁጥጥር የኘሮጀክት አፈጻጸም ወቅታዊ መረጃ ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ እንዲደርስና የሚመለከታቸው አካላት በኘሮጀክት ተግባራዊ አፈጻጸመ ያጋጠሙ ችግሮችን በውል ለይተው ለችግሮቹ ወቅታዊ መፍትሄ በመስጠት የአመራር ተልዕኮአቸውን በብቃት እንዲወጡ ዋነኛ ሚና ይጫወታል፡፡ በመሆኑም ክትትልና ቁጥጥር ስኬታማ የአመራር መሣሪያ ሆኖ እንዲያገለግል በሪፖርት፣ በመስክ የኘሮጀክት ግምገማና በመንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የጋራ መድረክ ግምገማ የሚኖረው ግንኙነት ፈጣን፣ ቀላልና ግልጽ ሆኖ ወቅታዊ የመረጃ ፍሰትና የምላሽ አሰጣጥ ሥርዓት ሊዘረጋለት ይገባል፡፡

CCRDA

5.1 ሪፖርት

ሪፖርት በፕሮጀክት አፈጻጸም ሂደት ፕሮጀክቱ የደረሰበትን የአፈጻጸም ደረጃ በአንድ በተወሰነ ወቅት የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራትን፣ ያጋጠሙ ችግሮችንና የተወሰዱ /ሊወሰዱ የሚገባቸውን የመፍትሄ ርምጃዎችን በሚመለከት ትክክለኛና ወቅታዊ መረጃ ለውሣኔ ሰጭ አካላት ለማቅረብ የሚያስችል አንድ የክትትልና ቁጥጥር መሣሪያ ነው።

የሪፖርት መዘግየት የፕሮጀክት ዋና ዋና ተግባሮች በታቀደላቸው ጊዜ እንዳይፈጸሙ ሊያጓትት፣ አጠቃላይ የፕሮጀክት የሥራ ፕሮግራም ሊያዛባ፣ የፕሮጀክት አፈጻጸም ከተቀመጠለት የአፈጻጸም አቅጣጫ ሊወጣና አላስፈላጊ የጊዜና የሐብት ብክነት ሊከተል ስለሚችል ወቅቱን የጠበቀ ሪፖርት የማቅረብ አስፈላጊነት በመያድ ተገቢ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

አመዝኮ የመያድን አጠቃላይ እንቅስቃሴ፣የፕሮጀክት የሥራ ክንውንና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮችን በቋሚነት የመከታተል ኃላፊነት አለበት። በመሆኑም የመያድ እንቅስቃሴ አጠቃላይ ሪፖርትና የመያድ የፕሮጀክት ክንውን ሪፖርት ወቅታቸውን ጠብቀው ለሚመለከተው የዞን፣ የክልል ወይም የፌዴራል አመዝኮ መቅረብ ይኖርባቸዋል።

5.1.1 የመያድ እንቅስቃሴ ጠቅላላ ሪፖርት /Status Report/

5.1.1.1 የመያድ ጠቅላላ ሪፖርት

የመያድ እንቅስቃሴ ጠቅላላ ሪፖርት /Status Report/ በየዓመቱ ጥር ወር የሚቀርብ ዓመታዊ ሪፖርት ነው። የዚህ ሪፖርት አጠቃላይ ዓላማ የሚመለከተውን መያድ የፕሮጀክት የሐብት ይዞታ መረጃ ለተፈራራሚ/ተጠቃሚ ወገኖች ማቅረብ ሲሆን፣ ለሚከተሉት መሠረታዊ ጉዳዮች ትኩረት ይሰጣል።

ሀ. ጠቅላላ የተንቀሳቀሰ ሐብት በዓይነትና በጥሬ ገንዘብ፣

ለ. የተንቀሳቀሰ ሐብት በለጋሽ ድርጅት፣ በተገኘበት ቀን፣ በዓላማና በዓይነት፣

ሐ. ቃል የተገባለት ሐብት በለጋሽ ድርጅቶች፣ ይደርሳል ተብሎ በሚገመትበት ቀን፣ በዓላማና ዓይነት

መ. ሊገኝ የሚችል ሐብት በምንጭ

ሠ. ከሪፖርት ዓመቱ በፊት ለአንድ ዓመት የተከናወኑ ፕሮጀክቶች/ፕሮግራሞች

ረ. በሂደት ላይ ያሉ ፕሮጀክቶች/ፕሮግራሞች

ሰ. ለዘመኑ የታቀዱ ፕሮጀክቶች/ፕሮግራሞች

CCRDA

ሸ. የአሠራር የአቅጣጫ ለውጥ

ቀ. የመያድ ቀልፍ አመራር አካላት ለውጥ

በ. ቋሚና የኮንትራት ሠራተኞች በትምህርት ዝግጅት፣ በዜግነትና በሙያ ደረጃ

ተ. ሌሎች ጠቃሚ መረጃዎች ሊካተቱ ይችላሉ።

5.1.1.2 <u>የመያድ የቋሚ ንብረት ሪፖርት</u>

የመያድ የቋሚ ንብረት ሪፖርት በእያንዳንዱ አዲስ በጀት ዓመት መጀመሪያ ጥር ወር የሚቀርብ ሆኖ የሚከተሉትን ያካትታል።

ሀ. ጠቅላላ የተሽከርካሪዎች ብዛት በዓይነት፣ በአቅምና በይዘት ደረጃ(condition) ወዘተ ...

ለ. ለኘሮጀክት የተመደቡ ተሽከርካሪዎች ብዛት

ሐ. የማሽን ወይም ሌሎች ዕቃዎች ዓይነት፣ የሚገኙበት ቦታ፣ አቅምና የይዘት ደረጃ

መ. ሌሎች ቋሚ ዕቃዎች (ጋራዥ፣ መጋዘን ወ.ዘ.ተ) በቦታና በአቅም

ሠ. የጽሕፈት ቤት ማቴሪያሎች ግምት በብር

ረ. ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች

5.1.1.3 <u>የመያድ የክምችት ሪፖርት</u>

የመያድ የክምችት ሪፖርት በየወሩ ለዞን ወይም ለክልል አመዝኩ ጽ/ቤቶች የሚቀርብ ሪፖርት ነው። ሪፖርቱ ከምግብ፣ ከመድሃኒትና ከቫይታሚኖች ወዘተ ... ጋር ለተዛመደ ክምችት ተገቢ ትኩረት ይሰጣል።

የመያድ የክምችት ሪፖርት ይዘት የሚከተሉትን መሠረታዊ ጉዳዮች ያካተተ መሆን ይኖርበታል።

ሀ. በወሩ መጀመሪያ የነበረ ክምችት መጠን

ለ. በወሩ ገቢ የተደረገ አቅርቦት መጠን

ሐ. በወሩ የተሠራጨ መጠን

መ. በወሩ በብልሽት ምክንያት ከጥቅም ውጭ የሆነ መጠን

ሠ. በወሩ ሥራ ላይ ያልዋለ ቀሪ የክምችት መጠን

በአስቸኳይ አደጋ ጊዜ የክምችት ሪፖርት በየግምንቱ የሚቀርብበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል።

CCRDA

5.1.1.4 <u>የመያድ የሐብት አጠቃቀም ሪፖርት/ Resource Utilization Report/</u>

የመያድ የሐብት አጠቃቀም ሪፖርት በየዓመቱ ለኘሮጀክት ተጠቃሚዎችና ለኘሮጀክት ተፈራራሚዎች በጥር ወር የሚቀርብ ሆኖ ሪፖርቱ የሚከተሉትን ሊያካትት ይገባል፡፡

ሀ. ባለፈው ዓመት የወጣ ጠቅላላ ወጭ

ለ. ወጭዎች በኘሮጀክት/በኘሮግራምና በሥራዎች

ሐ. አስተዳደራዊ ወጭ /Overhead cost/

መ. በኘሮጀክት ፍጻሜ ምክንያት ለሌሎች የመንግሥት አስፈጻሚ አካላት የተዛወሩ መሣሪያዎች፣ ተሽከርካሪዎችና ሌሎች ንብረቶች

ሠ. በድርጊት መርሃ ግብሩ መሠረት ሥራ ላይ ያልዋለ ሐብት(unutilized resource)

ረ. በሐብት አጠቃቀም ላይ የተከሰቱ ቁልፍ ችግሮች

ሰ. ሥራ ላይ ያልዋለ ንብረት በዓይነትና በአጠቃቀም ዕቅድ

5.1.1.5 <u>የመያድ የሂሣብ ምርመራ ሪፖርት</u>

ሀ. የመያድ የኘሮጀክት ሐብት አጠቃቀም ሥርዓት ተቀባይነት ያለው የሂሣብ አያያዝ መርህን የጠበቀ መሆን ይኖርበታል፡፡

ለ. የመያድን ሂሣብ መቆጣጠርና ማስመርመር የአመዝኮ ኃላፊነት በመሆኑ መያድ ዓመታዊ የሂሣብ ምርመራ ሪፖርት እንዲያቀርቡ ይጠየቃሉ፡፡

ሐ. የመያድ ኘሮጀክቶች ዓመታዊ የሂሣብ ምርመራ በጠቅላይ ኡዲት ዕውቅና ተሰጥቷቸው በአመዝ ኮሚሽንና በመያድ የጋራ ስምምነት በሚመረጡ የሂሣብ መርማሪ ድርጅቶች አማካኝነት ይካሄዳል፡፡

መ. በሂሣብ ምርመራ ወቅት መያድ ሕጋዊ የሂሣብ ማስረጃዎችን፣ ከአመዝ ኮሚሽንና ከሌሎች ሴክተሮች ጋር የተፈፀሙ የስምምነት ውሎችን፣ በማቅረብ ሂሣባቸውን ማስመርመርና አስፈላጊውን የሂሣብ ምርመራ ወጪ መሸፈን አለባቸው፡፡

ሠ. የሂሣብ ምርመራ ሪፖርት እያንዳንዱ የበጀት ዓመት ከተጠናቀቀ በ6ወራት ጊዜ ውስጥ ለአመዝ ኮሚሽን መቅረብ ይኖርበታል፡፡

ረ. በመያድ ኘሮጀክት አፈጻጸም ላይ ችግር ሊኖር እንደሚችል ከተገመተ አመዝ ኮሚሽን ከመያድ ጋር የተስማማበትን የምርመራ ጊዜ ሳይጠብቅ፣በማንኛውም ጊዜ ምርመራው እንዲካሄድ ሊያደርግ ይችላል፡፡

CCRDA

5.1.2 የመያድ የኘሮጀክት ክንውን ሪፖርት

5.1.2.1 የሩብ ዓመትና ዓመታዊ የኘሮጀክት የክንውን ሪፖርት

- በኘሮጀክት አፈጻጸም የሚሠማሩ መያድ በሩብ ዓመትና፣ በዓመታዊ ሪፖርቶቻቸው የኘሮጀክት ዋና ዋና ተግባራትና / physical activities /የበጀት /financial/ አፈጻጸም ክንውኖቻቸውን ከድርጊት መርሃ ግብራቸውና/ዕቅዳቸው/ ስምምነት ከተፈጸመበት ኘሮጀክት ኘሮግራም ጋር በማነፃፀር ለሚመለከታቸው የኘሮጀክት ተፈራራሚዎችና በየደረጃው ላሉት የኘሮጀክት ተጠቃሚ የሴክተር መ/ቤቶች በወቅቱ የማቅረብ ግዴታ አለባቸው፡፡
- የኘሮጀክት አፈጻጸም የሩብ ዓመት ሪፖርት ለሁሉም የኘሮጀክት ተፈራራሚ አካላትና በየደረጃ ላሉ የኘሮጀክት ተጠቃሚዎች እያንዳንዱ ሩብ ዓመት በተጠናቀቀ በ15 ቀናት ጊዜ ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡
- የኘሮጀክት አፈጻጸም ዓመታዊ ሪፖርት የበጀት ዓመቱን የኘሮጀክት አፈጻጸም የሚያመለክት ሪፖርት ሆኖ በየደረጃው ለሚገኙ ተፈራራሚ መ/ቤቶችና የመስተዳድር አካላት እያንዳንዱ የበጀት ዓመት በተጠናቀቀ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡
- የክልሉ አመዝ ኮሚሽን የሩብ ዓመት የኘሮጀክት አፈጻጸም ሪፖርትም ሆነ ዓመታዊ የኘሮጀክት አፈጻጸም ሪፖርት በወቅቱ ለማያቀርቡ መያድ አስፈላጊ የእርምት ማሳሰቢያ ሊጽፍ ይችላል፡፡
- የሚመለከተው መያድ ተፈላጊውን ሪፖርት ለሁለት ተከታታይ ሩብ ዓመት ማቅረብ ካልቻለ ከሚመለከታቸው የኘሮጀክት ተፈራራሚዎችና በየደረጃው ካሉ አግባብ ያላቸው አካላት በተውጣጣ ቡድን የኘሮጀክት አፈጻጸም ግምገማ ተካሂዶ የግምገማውን ውጤት መሠረት ያደረገ ርምጃ ይወስዳል፡፡
- የሩብ ዓመት ሪፖርት ይዘት በአባሪ ቅጽ ___ በተመለከተው መሠረት መቅረብ ይኖርበታል፡፡

CCRDA

5.1.2.2 <u>የኘሮጀክት ማጠናቀቂያ ሪፖርት</u>

ሀ. ኘሮጀክት የመጀመሪያ ጊዜ እንዳለው ሁሉ የማጠናቀቂያ ጊዜ አለው፡፡ መያድ በኘሮጀክት ፍጻሜ ወቅት በኘሮጀክት ዘመን የተከናወኑ የኘሮጀክት ተግባራትን አፈጻጸም አስመልክቶ ለኘሮጀክት ተፈራራሚ ወገኖችና በየደረጃው ላሉት የኘሮጀክት ተጠቃሚዎች የኘሮጀክት ዘመኑ ከመጠናቀቁ አንድ ወር በፊት የኘሮጀክት ማጠናቀቂያ ሪፖርት ያቀርባሉ፡፡

ለ. የኘሮጀክት ዘመን መራዘም ወይም መቋረጥ ጉዳይ የኘሮጀክት ማጠናቀቂያ ሪፖርቱን ተከትሎ ተግባራዊ በሚሆነው የኘሮጀክት ማጠናቀቂያ ግምገማ/ project terminal evaluation/ ውጤት ይወሰናል፡፡

ሐ. የኘሮጀክቱን መጠናቀቅ ተከትሎ በኘሮጀክት ስምምነቱ መሠረት የሚመለከተው መያድ ኘሮጀክቱንና የኘሮጀክቱን ንብረት ለሚመለከታቸው ወገኖች ያስረክባል፡፡

መ. መያድና የሚመለከታቸው ተፈራራሚ ወገኖች ርክክብ የተፈጸመበትን ኘሮጀክት ቀጣይ ተግባር በማይጐዳ መልኩ የሚመለከተው መያድ የኘሮጀክቱን ንብረት በክልሉ ውስጥ ለሚያካሂደው ተመሳሳይ ኘሮጀክት በሚጠቀምበት ሁኔታ ላይ መደራደር ይችላሉ፡፡

- የመጠናቀቂያ ሪፖርት ቪጋር (terms of reference) በአባሪ __ ተመልክቷል፡፡

5.2 <u>የኘሮጀክት የመስክ ግምገማ</u>

የኘሮጀክት ግምገማ በኘሮጀክት አፈጻጸም ሂደት፣ በኘሮጀክት ግማሽ/መካከለኛ ዘመንና በኘሮጀክት ማጠናቀቂያ ወቅት የሚካሄድ የኘሮጀክት ክትትልና ቁጥጥር ዘዴ ነው፡፡

5.2.1 <u>በኘሮጀክት አፈጻጸም ሂደት የሚከናወን የኘሮጀክት ግምገማ/On going Project evaluation/</u>

በኘሮጀክት አፈጻጸም ሂደት የሚከናወን የኘሮጀክት ግምገማ ኘሮጀክቱ የታለመለትን ግብ ለማሳካት የተቀመጡትን የኘሮጀክት ዋና ዋና ተግባራት በተቀመጠለት የአፈጻጸም አቅጣጫ፣ ተፈላጊውን የጥራት ደረጃ ጠብቆ፣ በታቀደው ጊዜ ውስጥ እየተከናወነ መሆኑን በቅርብ በመመልከት የኘሮጀክቱን ጥንካሬና ድክመት በውል ለይቶ ችግሩን ለመፍታት መወሰድ የሚገባውን መፍትሄ በወቅቱ ለመወሰን የሚያስችል በመሆኑ ለኘሮጀክት ስኬታማ አፈጻጸም ጉልህ ሚና ይጫወታል፡፡ በመሆኑም የዞን አመዝኪ ቅ/ጽ/ቤቶች፣ የዞን የኘሮጀክት ተፈራራሚ/ተጠቃሚ

GCRDA

መምሪያዎች፣ የሚመለከተው መያድ፣የወረዳ መስተዳድር፣ የወረዳ የሴክተር መ/ቤቶችና ተጠቃሚው ህብረተሰብ / Stake holders/ የመያድ የኘሮጀክት አፈጻጸም ሂደት በኘሮጀክት ስምምነቱና በዓመታዊ የድርጊት መርሃ ግብሩ መሠረት እየተፈጸመ መሆኑን ለማረጋገጥ ተከታታይ የኘሮጀክት ግምገማ የማካሄድ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

5.2.2 <u>በኘሮጀክት ግማሽ ዘመን የሚከናወን የኘሮጀክት ግምገማ/mid term project evaluation/</u>

በኘሮጀክት መካከለኛ ዘመን የሚካሄድ የኘሮጀክት የግማሽ ዘመን ግምገማ (mid term project evaluation) የኘሮጀክቱን የግማሽ ዘመን አፈጻጸም በመገምገም በቀሪው ግማሽ የኘሮጀክት ዘመን መከናወን የሚገባቸውን ተግባራትና የበጀት አጠቃቀም ዝርዝር የአፈጻጸም አቅጣጫ ለመወሰን የሚያስችል የኘሮጀክት ክትትልና ቁጥጥር ተግባር ሲሆን፣ በኘሮጀክት አፈጻጸም ሂደት ከሚከናወኑት ዋነኛ ግምገማዎች አንዱ ነው፡፡

ይህ ተግባር በኘሮጀክቱ ቀሪ ዘመን ለኘሮጀክቱ ስኬታማነት ያለው ወሣኝነት ግምት ውስጥ ገብቶ የኘሮጀክት የግማሽ ዘመን ግምገማ /mid term evaluation/ ከሁሉም የኘሮጀክት ተፈራራሚዎች በየደረጃው ካሉት የኘሮጀክት ተጠቃሚ የበታች የሴክተር መ/ቤቶችና የወረዳ መስተዳድር ተወካዮችን በአባልነት በያዘ ቡድን የተጠቃሚው ሕዝብ ተወካዮችና የመያድ የኘሮጀክት ተጠሪዎች በተገኙበት የመስክ የኘሮጀክት ግምገማ ይካሄዳል፡፡

5.2.3 <u>የኘሮጀክት ማጠናቀቂያ ግምገማ /terminal project evaluation/</u>

በኘሮጀክት ማጠናቀቂያ ወቅት የሚካሄድ የኘሮጀክት ማጠናቀቂያ ግምገማ የኘሮጀክቱን የተጠናቀቁና ያልተጠናቀቁ ሥራዎች፣ የኘሮጀክቱን ብቃትና የጥራት ደረጃ፣ የሐብት አጠቃቀሙን ውጤታማነትና ኘሮጀክቱ አገልግሎት ለመጀመር በሚችልበት ደረጃ መሆን አለመሆኑን በውል በማጤን ለኘሮጀክቱ መቋረጥ ወይም መቀጠል ውሣኔ የሚያበቃ የክትትልና ቁጥጥር ተግባር ነው፡፡ ይህ ተግባር የኘሮጀክት ተፈራራሚዎች፣ የኘሮጀክት ተጠቃሚ የበታች የሴክተር መ/ቤቶችና የወረዳ መስተዳድር ተወካዮችን በአባልነት በያዘ ቡድን የተጠቃሚውን ህ/ሰብ ተወካዮችና የኘሮጀክት ተጠሪዎችን በሚያሳትፍ አግባብ ይፈጸማል፡፡

5.2.4 በሁሉም የኘሮጀክት ግምገማ የሕ/ሰብ ተሳትፎ ተገቢ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

5.2.5 መያድን የኘሮጀክት ግምገማ የማስተባበር ኃላፊነት ኘሮጀክቱ በተፈረመበት ደረጃ ያሉት የአመዝኰ አካላት ሲሆን፣ በወረዳ ደረጃ የተፈረመ ኘሮጀክት ግምገማን የማስተባበር ኃላፊነት የወረዳ መስተዳድር ይሆናል፡፡

CCRDA

5.2.6 ለኘሮጀክት ግምገማው የሚያስፈልገው ወጭ ለዚህ ተግባር ከተመደበው የኘሮጀክት በጀት ይሸፈናል። ሆኖም ግን ለኘሮጀክት ግምገማ የተመደበ የኘሮጀክት በጀት ከሌለ በግምገማው የሚሳተፉት ወገኖች ወጭውን በራሳቸው ይሸፍናሉ።

5.2.7 በኘሮጀክት ግምገማ ውጤት አለመስማማት ካጋጠመና እንደገና ግምገማ ማካሄድ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ግምገማው እንደገና እንዲካሄድ የጠየቁት ወገኖች ለግምገማው የሚያስፈልገውን ወጭ ሸፍነው እንደገና ግምገማ ሊካሄድ ይችላል።

5.2.8 የኘሮጀክት የመካከለኛ ዘመን የግምገማ ሪፖርትም ሆነ የኘሮጀክት ማጠናቀቂያ ግምገማ ሪፖርት ግምገማው በተጠናቀቀ በሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ ኘሮጀክቱን ለሚያስተባብረው የአመዝኮ ጽ/ቤት መቅረብ አለበት። ሪፖርቱ የደረሰው የአመዝኮ ጽ/ቤት ሪፖርቱን ከ5 የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለሚመለከታቸው ወገኖች ሁሉ በመሸኛ ይልካል።

5.3 <u>የመንግሥታዊ አካላትና የመያድ የጋራ መድረክ</u> /Gos-NGOs forum/

ሀ) መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በመካከላቸው ያለውን የልማት ትብብር በማጠናከር በመያድ ለሚተገበሩ ኘሮጀክቶች ስኬታማ አፈጻጸምና ለሕዝብ ተጠቃሚነት መረጋገጥ ተልዕኮአቸውን በአግባቡ እንዲወጡ በማስቻል የመንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የጋራ መድረክ (GOs – NGOs forum) ለኘሮጀክት ክትትልና ቁጥጥር ጉልህ አስተዋጽኦ ያበረክታል።

ለ) የመንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የጋራ መድረክ የመያድ ኘሮጀክትን የፊዚካል ሥራ ክንውንና የበጀት አጠቃቀም ከድርጊት መርሃ ግብሩ ጋር በማነፃፀር፣ የኘሮጀክት አፈጻጸሙን ወቅታዊነት፣ የሐብት አጠቃቀሙን ውጤታማነትና የሪፖርቱን ገላጭነት ይገመግማል።

ሐ) በመያድ ኘሮጀክቶች አፈጻጸም ያጋጠሙ ችግሮችን በውል በመለየት የጋራ መፍትሄ ይሰጣል።

መ) የሴክተር መ/ቤቶችም ሆነ የኘሮጀክት ፈጻሚ መያድ በኘሮጀክት አፈጻጸም ሂደት የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት በአግባቡ መወጣታቸውን ይገመግማል፣ የማስተካከያ ርምጃዎችን ይወስዳል።

CCRDA

5.3.1 <u>የወረዳ የመንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች መድረክ</u> <u>(Woreda GOs – NGOs forum)</u>

ሀ) በወረዳ ደረጃ የመንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የጋራ መድረክ ይኖራል፡፡

ለ) የወረዳ መንግሥታዊ አካላትና መያድ የጋራ መድረክ በወረዳ መስተዳድር ሰብሳቢነት የወረዳ የኘሮጀክት ተፈራራሚ/ተጠቃሚ የሴክተር መ/ቤቶችና በወረዳው ውስጥ የሚንቀሳቀሱ መያድ (operational NGOs) የጋራ መድረክ ሆኖ ያገለግላል፡፡

ሐ) በወረዳው ውስጥ የሚከናወነውን የመያድ ኘሮጀክቶች የአፈጻጸም ሂደት በጋራ ይገመግማል፡፡ ለአስተዳደራዊና ቴክኒካዊ ችግሮች የጋራ መፍትሄ ይሰጣል፡፡

መ) የጋራ መድረኩ የስብሰባ ጊዜ በወር ውስጥ አንድ ጊዜ ይሆናል፡፡

5.3.2 <u>የዞን የመንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች መድረክ /Zonal GOs - NGOs forum)</u>

ሀ. በዞን ደረጃ የመንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የጋራ መድረክ /Gos - NGOs forum/ ይኖራል፡፡

ለ. የዞን የጋራ መድረክ በዞን መስተዳድር ሰብሳቢነት በአመዝኮ ፀሐፊነት፣ በኘሮጀክት ተፈራራሚ /ተጠቃሚ የሴክተር መ/ቤቶች፣ በዞኑ ውስጥ በሚንቀሳቀሱ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና በኘሮጀክት ወረዳዎች የወረዳ መስተዳድር ተወካዮች አባልነት ይመሠረታል፡፡

ሐ. በዞኑ ውስጥ የሚከናወነውን የመያድ ኘሮጀክቶች አፈጻጸም በጋራ ይገመግማል፡፡ ለአስተዳደራዊና ቴክኒካዊ ችግሮች የጋራ መፍትሄ ይሰጣል፡፡

መ. የዞን የጋራ መድረክ የስብሰባ ጊዜ በየሩብ ዓመቱ አንድ ጊዜ ይካሄዳል፡፡

CCRDA

5.3.3 ክልላዊ የመንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች መድረክ / Regional Gos – NGOs forum/

ሀ. ክልላዊ የመያድና የመንግሥታዊ አካላት የጋራ መድረክ (Gos – NGOs forum) የክልሉ መስተዳድር፣ ተፈራራሚ/ተጠቃሚ የሴክተር ቢሮዎች፣ በክልሉ የሚንቀሳቀሱ መያድ፣ የዞን መስተዳድሮችና የዞን የኘሮጀክት ተፈራራሚ/ተጠቃሚ የሴክተር መ/ቤቶችን ያሳትፋል።

ለ. ክልላዊ የመያድ መድረክ ከተናጠል የኘሮጀክት አፈጻጸም ይልቅ ፖሊሲ፣ መመሪያና የአሠራር አቅጣጫዎች ለሚጠይቁ የጋራ ጉዳዮችና በአፈጻጸም ያጋጠሙ የጋራ መፍትሄ የሚያሻቸውን ችግሮች መፍትሄ በመስጠት ላይ ያተኩራል።

ሐ. የክልላዊው የጋራ መድረክ ስብሰባ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ይጠራል።

6. የመያድ ኘሮጀክት ርክክብ፣ የንብረት ሽያጭና የገቢ ማስገኛ ኘሮግራሞች አፈጻጸም

6.1 የመያድ ኘሮጀክት ርክክብ

ሀ. መያድ የኘሮጀክት ስምምነት ውል ተፈራርመው የሚተገብሯቸው ኘሮጀክቶች ሲጠናቀቁ በኘሮጀክት ስምምነቱ ወቅት ወይም ከዚያ በኋላ በተደረገ የጋራ ስምምነት በኘሮጀክት ተረካቢነት ከታወቁ የሕዝብ ተቋማት፣ ከሴክተር መ/ቤት ወይም ሌላ አካላት ጋር የኘሮጀክት ርክክብ ይፈጸማል።

ለ. የመያድ ኘሮጀክት ርክክብ ከመካሄዱ በፊት ሥራዎች በኘሮጀክት ስምምነቱ መሠረት ጥራታቸው ተጠብቆ መጠናቀቃቸውንና ለአገልግሎት ብቁ መሆናቸው ይረጋገጣል።

ሐ. ከርክክቡ በፊት ያልተጠናቀቁ ሥራዎች መኖራቸው ከታወቀ የሚመለከተው መያድ ለቀሪ ሥራዎች ማጠናቀቂያ የሚያስፈልገው ጊዜ ተወስኖ እንዲጠናቀቁ ይደረጋል።

መ. የመያድ ኘሮጀክት ርክክብ በስምምነት የተካተቱ መያድ ለኘሮጀክት ማስፈጸሚያ ይገለገሉባቸው የነበሩ እንደ ተሽከርካሪ፣ ማሽነሪዎችና ሌሎች ቋሚና አላቂ ዕቃዎች ርክክብን ያካትታል።

ሠ. ኘሮጀክት አስረካቢው መያድ በዚያው ወረዳ ውስጥ ቀጣይ ለኅብረተሰብ አገልግሎት የሚሰጡ ኘሮጀክቶችን ለመተግበር የሚንቀሳቀስ ከሆነ ርክክብ የተፈጸመበትን ኘሮጀክት የሥራ እንቅስቃሴ እስካላደናቀፈ ድረስ በኘሮጀክት ተፈራራሚዎች ስምምነት ርክክብ የተፈጸመበትን ኘሮጀክት ንብረቶቹ መጠቀም ይችላል።

CCRDA

ረ. የመያድ የኘሮጀክትና የኘሮጀክት ንብረት ርክክብ ከኘሮጀክት ተፈራራሚዎች ፣ በየደረጃው ካሉት የኘሮጀክት ተጠቃሚ የሴክተር መ/ቤቶች፣ ከወረዳ መስተዳድር፣ ከሚመለከተው መያድና ከህብረተሰብ ተወካዮች በተመሠረተ የርክክብ ኮሚቴ አማካኝነት ይፈጸማል።

የኘሮጀክትና የኘሮጀክት ንብረት ርክክቡ ሠነድ ለሁሉም ተፈራራሚ የኘሮጀክት ተፈራራሚዎች፣ ለአስረካቢና ተረካቢ ወገኖች ይሰጣል።

6.2 በዓይነት የሚገኝ የመያድ ንብረት ሽያጭ /Sale of commodities by NGO/

ሀ. መያድ ከጥሬ ገንዘብ ሌላ ለኘሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚያገለግሉ ንብረቶች ፣ የምግብ እህልና ዘይት ከረጅ ድረጅቶቻቸው እገዛ ሊያገኙ ይችላሉ። እነዚህ እገዛዎች በዓይነት ወይም በገንዘብ ተቀይረው ለኘሮጀክት ማስፈጸሚያ አገልግሎት ይውላሉ። የተለገሰው እገዛ በቀጥታ ለኘሮጀክት ተጠቃሚዎች ሊውል ወይም የመንግሥት የጨረታ ሽያጭ ደንብና ሥርዓት በሚፈቅደው መሠረት ወደ ገንዘብ ተቀይሮ ለኘሮጀክት ማስፈጸሚያ ሊውል ይችላል።

ለ. ማናቸውም ከውጭ ሐገር በዓይነት የሚገቡ ንብረቶች በቅድሚያ በኘሮጀክት ሠነድ ውስጥ በግልጽ ተለይተው ሊጠቀሱና በሁሉም የኘሮጀክት ተፈራራሚ አካላት አስፈላጊነታቸው ታምኖበት በኘሮጀክት ስምምነት የተካተቱ መሆን አለባቸው።

ሐ. በዓይነት ተለግሰው ገበያ ላይ የሚሸጡ ንብረቶች ወደሐገር ውስጥ መግባት የሚችሉት በአገር ውስጥ ገበያ ተፈላጊነት ያላቸው መሆኑ ሲረጋገጥና ከመንግሥት ፈቃድ ሲያገኙ ይሆናል።

መ. በዓይነት የተገኘ የመያድ ንብረት ሽያጭ እንደገበያው አመችነት በማዕከል ወይም በክልል ደረጃ የሚፈጸም ሆኖ ከአመዝኩ፣ ከሚመለከተው መያድና ከፋይናንስ በሚመሠረት የጨረታ ኮሚቴ አማኻኝነት በአመዝኩ አስተባባሪነት ይፈጸማል።

6.3 የመያድ ገቢ ማስገኛ ኘሮግራሞች

ሀ. መያድ ለትርፍ የተቋቋሙ ድርጅቶች ባለመሆናቸው ከአመዝኩ ፈቃድ ካልተሰጣቸው በስተቀር በንግድና በሌላ ትርፍ በሚያስገኝ መስክ መሠማራት አይችሉም። ሆኖም ግን መያድ ለሕብረተሰቡ አገልግሎት የሚሰጡ ኘሮጀክቶችን ለመተግበር፣ ለአካባቢ ተፈጥሮ ሐብት ጥበቃ አስተዋጽኦ በሚያበረክቱ እንደችግኝ አፍልቶ መሸጥ፣ ደን ልማትና አትክልትና ፍራፍሬ ሽያጭ በሚገኝ ገቢ ለህ/ሰብ አገልግሎት የሚሰጡ ኘሮጀክቶችን ለመተግበር ከአመዝኩ ፈቃድ ማግኘት ይችላሉ።

CCRDA

ለ. መያድ ገቢ በሚያስገኙ መስኮች የሚሰማሩ ከሆነ በየደረጃው ያሉ የአመዝኩ አካላት በመያድ የሚሰበሰበው ገቢ በአግባቡ እየተመዘገበ ሂሣቡ በየጊዜው ታውቆ የሚሰበሰብ መሆኑን በቅርብ የመከታተልና የመቆጣጠር ኃላፊነት አለባቸው፡፡

ሐ. በገቢ ማስገኛ ፕሮግራሞች ለመሠማራት ፍላጐት ያላቸው መያድ የሚሠማሩበትን አካባቢ፣ የገንዘብ ምንጫቸውንና የሚገኘው ገቢ በምን ተግባር ላይ እንደሚውል በመግለጽ ለአብክመ አመዝኩ ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ፡፡

መ. የአብክመ አመዝኩ ከመያድ ጥያቄ እንደቀረበለት የፕሮጀክት ሠነዱን ተመልክቶ የሚደርስበትን ውሣኔ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በጽሁፍ ለጠያቂው መያድ ያሳውቃል፡፡

ሠ. የአብክመ አመዝኩ ከመያድ የቀረበው የገቢ ማስገኛ ፕሮግራም አሳማኝ ሆኖ ሲያገኘው ፈቃድ የተሰጠውን መያድ ስም፣ አድራሻና የምዝገባ መለያ ቁጥር፣ የገቢ ማስገኛውን አይነትና ተግባራዊ የሚሆንበትን አካባቢ በመግለጽ ከሁለት ዓመት ላልበለጠ ጊዜ የሚያገለግል ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፡፡

ረ. በገቢ ማስገኛ ፕሮግራሞች የሚሠማሩ መያድ ራሱን የቻለ የሂሣብ መዝገብ የመያዝና የሩብ ዓመት የክንውን ሪፖርትና በኦዲተር የተመረመረ ዓመታዊ የሂሣብ ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ አለባቸው፡፡

ሰ. መያድ ከገቢ ማስገኛ ፕሮግራሞች የተገኘን ገቢ በተፈራራሚ ወገኖች የጋራ ስምምነት ለአቅም ግንባታ አገልግሎት፣ በሥራ ላይ ያሉ የፕሮጀክት እንቅስቃሴዎችን ለማስፋፋትና አዲስ ፕሮጀክቶችን ለመተግበር ሥራ ላይ ይውላል፡፡

ሸ. ከገቢ ማስገኛ ፕሮግራሞች የተገኘን ገቢ ስምምነት ላይ ላልተደረሰበት ማንኛውም አገልግሎት መጠቀም የፈቃድ መሠረዝንና በሕግ መጠየቅን ያስከትላል፡፡

7. <u>የመንግሥትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አጠቃላይ ኃላፊነቶችና ግዴታዎች</u>

7.1 <u>የመያድ ኃላፊነቶችና ግዴታዎች</u>

በዚህ መመሪያ ልዩ ልዩ ክፍሎች ከተካተቱት የመያድ ኃላፊነቶችና ግዴታዎች በተጨማሪ መያድ በልዩ ልዩ የክልሉ አካባቢዎች በሚያካሂዱት የፕሮጀክት እንቅስቃሴ የሐገሪቱንና የክልሉን ሕጐችና ደንቦች፣ የፕሮጀክት ስምምነታቸውንና ይህን መመሪያ የማክበርና መንግሥትና ሕዝብ የአደጋ ተጋላጭነትን ለመቀነስና ልማትን ለማፋጠን የሚያደርጉትን ጥረት ለማገዝ መንቀሳቀስ አለባቸው፡፡ መያድ በፕሮጀክት/ፕሮግራም አፈጻጸም ሂደት፡-

- አስተዳደራዊ ወጭን መቀነስ
- የሚያገኙትን ገቢ የማሳወቅ

CGRDA

- ሐብትን በብቃትና ውጤታማ በሆነ መንገድ መጠቀም
- የውጭ የኘሮጀክት ተቀጣሪዎችን ቁጥር መቀነስ
- የሥራ ድግግምንና በአንድ አካባቢ መሰባሰብን ማስወገድ
- ከሕብረተሰቡ ጋር መሥራት
- የልማት ዕድል ላላገኙና ለሩቅ አካባቢዎች የቅድሚያ ትኩረት መስጠት
- የሕብረተሰቡንና የመንግሥትን የአቅም ግንባታ ሂደት ማፋጠን
- የአደጋን መሠረታዊ መንስዔዎች ለማጥፋት መሥራት
- የሥራ አፈጻጸማቸውን በየጊዜው ሪፖርት ማድረግ
- ለሴቶች ተገቢ ትኩረት መስጠት ወዘተ

ትኩረት መስጠት አለባቸው፡፡

- መያድ የኘሮጀክት ማስተባበሪያ ጽ/ቤት እንዳስፈላጊነቱ በኘሮጀክቱ አካባቢ በማቋቋም ተፈላጊውን የሰው ኃይልና ማቴሪያል አሟልቶ ያደራጃል፡፡

7.2 የመንግሥት ግዴታዎችና ኃላፊነቶች

7.2.1 የመንግሥት ግዴታዎች

ሀ. በየትኛውም ደረጃ ያሉ የመንግሥት አካላት ለመያድ ሥራ ስኬታማነት ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣሉ፡፡

ለ. በአማራ ብሔራዊ ክልል የሴክተር መ/ቤቶችና በመያድ መካከል ያለውን ትብብር ለማጠናከር ተገቢ ትኩረት ይሰጣል፡፡

ሐ. መንግሥትና ኅብረተሰቡ የሚያካሂዱትን የማኅበረ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ለመደገፍ መያድን የሚያበረታቱና የልማት ሂደቱን የሚያፋጥኑ አጠቃላይ መመሪያዎችን ያወጣል፡፡

መ. እያንዳንዱ የኘሮጀክት ተፈራራሚ/ተጠቃሚ ቢሮና የዞን መምሪያ የመያድ ሥራን የሚያስተባብር ሙያተኛ (focal person) ይመድባል፡፡

ሠ. መንግሥት የመያድ ኘሮጀክት ዕቃዎች ከውጭ ከቀረጥ ነፃ እንዲገቡ ይፈቅዳል፣ ለኘሮጀክትና ለኘሮጀክት ማስባበሪያ ጽ/ቤት አገልግሎት አስፈላጊውን መሬት በነፃ ይሰጣል፣ በኘሮጀክቱ አፈጻጸም ከተፈራራሚ የሴክተር መ/ቤቶች የሚጠበቀውን የሙያተኛ ድጋፍ ያስተባብራል፡፡

CGRDA

ረ. የክልሉ መንግሥት በክልሉ ውስጥ ለሚመሠረቱ መያድ ዕድገትና ጥንካሬ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፡፡

ሰ. በመንግሥት አካላትና በመያድ መካከል ያለውን ትብብር ለማጠናከርና የመንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የትብብር ኮሚቴ በየደረጃው ይመሠርታል፡፡

ሸ. በመያድ እንቅስቃሴ የሚያጋጥሙ አስተዳደራዊና ቴክኒካዊ ችግሮችን በኃላፊነት ይፈታል፡፡

7.2.2 <u>የመንግሥት ኃላፊነቶች</u>

መያድ ከኘሮጀክት ስምምነት ውጭ የሆኑ ተግባሮች ሲፈጽሙና የሕዝብንና የሐገርን ጥቅም የሚጻረሩ ሆነው ሲገኙ አመዝኮ የሚከተሉትን የመፈጸም ኃላፊነትና መብት አለው፡፡

- በጥፋት ላይ የተገኘ መያድ ወይም የመያድ ተቀጣሪ ሠራተኛ እንቅስቃሴን የመመርመር/የማስመርመር
- ጥፋት የፈጸመውን መያድ ሂሣብ የመመርመር/ የማስመርመር
- ምርመራው እስኪጣራ ከእንቅስቃሴ የማገድ
- የምርመራ ውጤቱን ለሚመለከተው ለጋሽ ድርጅት/Donor/ የማሳወቅ
- የሐገሪቱን ሕግ በተጻረረ ወይም የኘሮጀክት ገንዘብ ባባከነ የመያድ ተቀጣሪ ግለሰብ ላይ ክስ የመመሥረት
- ማንኛውም መያድ ስህተት መሥራቱ ከተረጋገጠና ሥራውን መቀጠል የማያስችለው ሆኖ ከተገኘ የኘሮጀክት ውል መሠረዝና የሥራ እንቅስቃሴውን ማቋረጥ
- የመያድ ተቀጣሪ የውጭ ዜጋ በከፍተኛ ጥፋት ላይ ሲገኝ የሥራ ፈቃዱ እንዲሠረዝና ከሐገር እንዲወጣ ማስወሰን
- በመያድ የሥራ እንቅስቃሴ ላይ አጠቃላይ ግምገማ ማካሄድና የሚመለከተው መያድ እንቅስቃሴው እንዲቀጥል ወይም እንዲቋረጥ መወሰን

በኘሮጀክት ግምገማ የመያድን የኘሮጀክት ውል መቋረጥን ወይም ሌሎች መብቶችን ማጣት የሚያስከትሉ ጉድለቶች፡-

- የመንግሥት ደንብና ሕጐችን መጣስ
- ስምምነት የተፈጸመባቸውን ኘሮጀክቶች መተግበር አለመቻል
- ከመያድ የአሠራር መርህ መውጣት
- በሐብት አጠቃቀም፣ በአመራርና በቴክኒክ ብቃት ስምምነትን ጠብቆ አለመሥራት
- ሚዛናዊ ያልሆነ የበጀት አጠቃቀም

CCRDA

- የአደጋ ተጋላጭነትን ለመቀነስ፣ የፕሮጀክት ቀጣይነትን/sustainability/ ለማረጋገጥና በአቅም ግንባታ መስክ ባለው ሚና
- ስምሪቱ ከልማት ጋር ያለው ትስስር
- ሥራ የመፍጠር ዕድሉ

እነዚህን መመዘኛዎችና ሌሎች ሀቆችን መነሻ በማድረግ የመያድ የሥራ እንቅስቃሴ እየተመዘነ የመያድ የሥራ ፈቃድ /Operational agreement/ በየሶስት ዓመቱ ይታደሳል።

7.3 <u>የመንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የትብብር ኮሚቴ አመሠራረት</u>

ሀ. የመንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የትብብር ኮሚቴ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የበላይ ጠባቂነት ይመሠረታል።

ለ. የመንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የትብብር ኮሚቴ በመያድና በክልል ቢሮዎች፣ በዞንና በወረዳ የሴክተር መ/ቤቶችና በመስተዳድር አካላት መካከል ያለውን ትብብር በበላይነት ይመራል።

ሐ. የትብብር ኮሚቴው መያድ የሚያቀርቡትን ቅሬታ አጣርቶ ውሣኔ የመስጠት ሥልጣን አለው።

መ. በየደረጃው የሚቋቋመው የመያድ የትብብር ኮሚቴ በመያድ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም የሴክተር መ/ቤቶች ኃላፊነታቸውን በተገቢው መንገድ መወጣታቸውን በበላይነት ይቆጣጠራል።

ሠ. የመንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የትብብር ኮሚቴ ከክልል እስከወረዳ ባሉት የመስተዳድር ዕርከኖች ይዋቀራል።


ረ. የትብብር ኮሚቴው ተጠሪነት በየመስተዳድር ዕርከኑ ለሚገኘው የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚቴ ይሆናል።

ሰ. የትብብር ኮሚቴው በክልል ደረጃ በአመዝኮ ኮሚሽነር፣ በዞን ደረጃ በዞን ም/ሊቀመንበር /ማኅበራዊ ዘርፍ ኃላፊ፣ በወረዳ ደረጃ በወረዳ መስተዳድር ሊቀመንበር / ም/ሊቀመንበር ሰብሳቢነት ይመራል።

CCRDA

7.3.1 የመንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች

የትብብር ኮሚቴ መዋቅር



CCRDA

7.3.2 <u>የክልል የመንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የመንግሥት ትብብር ኮሚቴ</u>

7.3.2.1 <u>አባላት</u>

የክልል የመንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የትብብር ኮሚቴ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡፡

1ኛ. የክልሉ አመዝ ኮሚሽን ኮሚሽነር .... ሰብሳቢ
2ኛ. የግብርና ቢሮ ኃላፊ ..... አባል
3ኛ. የጤና ቢሮ " " ..... "
4ኛ. የትምህርት " " .... "
5ኛ. የውሃ ማዕ/ኢ/ሃ/ል ቢሮ ኃላፊ .... "
6ኛ. የሠ/ማ/ጉ / " " .... "
7ኛ. የዘ/ግ/አ/ተ/ኮ ኮሚሽነር .... "
8ኛ. የሕ/ሥ/ማ/ማ/ ቢሮ ኃላፊ .... "
9ኛ. የኘላንና ኢ/ል/ " " ..... "
10ኛ. ን/ኢ/ል/ " " .... "
11ኛ. የሴቶች ጉዳይ ጽ/ቤት " .... "
12ኛ. የምግብ ዋስትና ጽ/ቤት " ..... "
13ኛ. በመያድ የሚወክሉ የ3 አገር በቀልና
የ4ዓለም አቀፍ መያድ ተወካዬች ..... "
14ኛ. በአመዝ ኮሚሽን የቅ/ማስ/ኘላንና
መያድ ማስተ/ መምሪያ ኃላፊ ... . አባልና ፀሐፊ
15ኛ. ሌሎች አካላት እንዳስፈላጊነቱ አባል ሊሆኑ ይችላሉ

7.3.2.2 <u>የክልል የትብብር ኮሚቴ የስብሰባ ጊዜና አሠራር</u>

ሀ. የክልሉ የመያድና የመንግሥት ትብብር ኮሚቴ ቢያንስ በዓመት 4 ጊዜ ስብሰባ ያካሂዳል፡፡
ለ. የትብብር ኮሚቴው በየዓመቱ ለሚካሄደው የመንግሥታዊና መንግሥታዊ ያለሆኑ ድርጅቶች የጋራ መድረክ አጀንዳዎችን ያዘጋጃል፡፡
ሐ. ኮሚቴው አስቸኳይ ውሣኔ የሚሹ ጉዳዮች ሲያጋጥመው አስቸኳይ ስብሰባ መጥራት ይችላል፡፡
መ.የትብብር ኮሚቴው የራሱን የውስጥ አሠራር ደንብ ያወጣል፡፡
ሠ. በማናቸውም ጉዳይ የሚሰጥ ውሣኔ በብዙሃን ድምጽ ይወሰናል፡፡

CCRDA

7.3.3 <u>የዞን የመንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የመንግሥት ትብብር ኮ</u>ሚቴ

7.3.3.1 <u>አባላት</u>

በዞን ደረጃ የሚቋቋመው የመያድና የመንግሥት የትብብር ኮሚቴ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡፡

1ኛ. የዞን ም/ሊቀመንበር/ማኅበራዊ ዘርፍ ኃላፊ .....ሰብሳቢ
2ኛ. የዞኑ አመዝ ኮሚሽን ቅ/ጽ/ቤት ኃላፊ ..... ፀሐፊ
3ኛ. ግብርና መምሪያ ኃላፊ ..... አባል
4ኛ. ጤና " " ..... "
5ኛ. ትምህርት " " ..... "
6ኛ. ውሃ/ማዕ/አ/ሃ/ል መምሪያ ኃላፊ ..... "
7ኛ. ሠ/ማ/ጉ/ " " ..... "
8ኛ. የዘ/ባ/አ/ተ/ኮ/ማ/ጽ/ቤት " ..... "
9ኛ. የኘ/ኢ/ል/ መምሪያ " ..... "
10ኛ. የሕ/ሥ/ማ/ማ/ " " ..... "
11ኛ. የን/ኢ/ል " " ..... "
12ኛ. የሴቶች ማኅበር ጽ/ቤት " ..... "
13ኛ. የምግብ ዋስትና ጽ/ቤት " ..... "
13ኛ. በዞኑ በሚንቀሳቀሱ መያድ የሚወክሉ የ3 አገር በቀልና
የ4ዓለም አቀፍ መያድ ተወካዬች..... "
14ኛ. በአመዝ ኮሚሽን ቅ/ጽ/ቤት የመያድ ማስተ.ቡ/መሪ ..... አባል
15ኛ. ሌሎች አካላት እንደስፈላጊነቱ አባል ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

7.3.3.2 <u>የዞን የትብብር ኮሚቴ የስብሰባ ጊዜና አሠራር</u>

ሀ. የዞን የመያድና የመንግሥት የትብብር ኮሚቴ ቢያንስ በዓመት 4 ጊዜ ስብሰባ ያካሂዳል

ለ. የሩብ ዓመት የመያድ የጋራ መድረክ አጀንዳዎችንና ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን ለጋራ መድረኩ ያቀርባል፡፡

ሐ. መደበኛ የስብሰባ ጊዜ የማይጠብቅ አስቸኳይ ጉዳይ ሲያጋጥም የትብብር ኮሚቴው አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡

መ.የመንግሥት አካላትና የመያድ የጋራ መድረክ ስብሰባ መጥራት የሚጠይቅ ሁኔታ ሲኖር አስቸኳይ ስብሰባ መጥራት ይችላል፡፡

ሠ. የትብብር ኮሚቴው የውሣኔ አሰጣጥ ሥርዓት በብዙሃን ድምጽ ይሆናል፡፡

CCRDA

7.3.4 የወረዳ የመያድና የመንግሥት የትብብር ኮሚቴ

7.3.4.1 አባላት

በወረዳ ደረጃ የሚቋቋመው የመያድና የመንግሥት የትብብር ኮሚቴ ከወረዳ መስተዳድር፣ ከኘሮጀክት ተጠቃሚ የወረዳ የሴክተር መ/ቤቶችና በወረዳው ውስጥ በሥራ የተሠማሩ መያድ ተወካዮችን በማካተት ይዋቀራል፡፡

1ኛ. የወረዳ ሊቀመንበር/ም/ሊቀመንበር ..... ሰብሳቢ
2ኛ. የወረዳው ግ/ጽ/ቤት ኃላፊ ..... አባልና ፀሐፊ
3ኛ. የወረዳው ጤና ጽ/ቤት ኃላፊ ..... አባል
4ኛ. ወረዳው ትምህርት ጽ/ቤት ኃላፊ ..... አባል
5ኛ. የወረዳው ውሃ ጽ/ቤት ..... አባል
6ኛ. የወረዳው ሕ/ሥራ ማጎበራት ማስ/ጽ/ቤት ..... አባል
7ኛ. የወረዳ ምግብ ዋስትና ጽ/ቤት ..... አባል
8ኛ. የወረዳ የሴቶች ማጎበር ጽ/ቤት ..... አባል
9ኛ. በወረዳው የሚገኙ መያድ ..... አባላት
10ኛ. ሌሎች በወረዳው የሚገኙ አካላት እንዳስፈላጊነቱ አባል ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

7.3.4.2 የወረዳ የትብብር ኮሚቴ የስብሰባ ጊዜና አሠራር

ሀ. የወረዳ የመንግሥትና የመያድ የትብብር ኮሚቴ በወር አንድ ጊዜ ስብሰባ ያካሂዳል፡፡

ለ. ለወርሃዊ የወረዳ የመያድ የጋራ መድረክ አጀንዳዎችንና ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን ለይቶ ለውይይት ያቀርባል፡፡

ሐ. በወረዳው የመያድ ኘሮጀክቶችን አፈፃፀም በየሩብ ዓመቱ በመስክ ዕይታ የተደገፈ ግምገማ በማካሄድ የግምገማ ውጤቶችን ለዞኑ አመዝ ቅ/ጽ/ቤት ያቀርባል፡፡

መ. በወረዳው በመንግስት የሴክተር ጽ/ቤቶች የኘሮጀክት ተጠቃሚ ሕዝብና በመያድ ቅንጅት የሥራ ሂደት የሚፈጠሩ ችግሮችን ፈትሾ ወቅታዊ መፍትሄ ይሰጣል፣ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያደርጋል፡፡

ሰ. በወረዳው በሚካሄዱ የመያድ ኘሮጀክቶች አፈጻጸም ላይ ተጠቃሚው ሕዝብ ሙሉ ተሳትፎ እንዲረጋገጥ በበላይነት ያስተባብራል፡፡

CCRDA

ረ. በወረዳው ለሚሠሩ መያድ ምቹ የሥራ ሁኔታ እንዲፈጠር አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰማል፡፡

ሰ. መደበኛ የስብሰባ ጊዜ የማይጠብቅ አስቸኳይ ጉዳይ ሲያጋጥም የትብብር ኮሚቴው አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡

ሸ. የትብብር ኮሚቴው የውሣኔ አሰጣጥ ሥርዓት በብዙሃን ድምጽ ይወሰናል፡፡

CCRDA

ቅጽ-ዓፅ 1

የመያድ ዓመታዊ ዕቅድ /NGO's annual plan of operation/

የኘሮጀክቱ መሠረታዊ መረጃዎች ማሰፈሪያ ቅጽ

1. የኘሮጀክቱ ስም_____
2. የኘሮጀክቱ ኮድ_____
3. ዕርዳታ ሰጭ/ስም_____
4. ኘሮጀክቱ የሚገኝበት ቦታ ክልል_____
   ዞን_____
   ወረዳ_____
   ቀበሌ_____
5. አስፈጻሚ መ/ቤት(ተፈራራሚ መ/ቤት) _____
6. ፈጻሚ መ/ቤት _____
7. ኘሮጀክቱ የተፈረመበት ቀን/ወር/ዓ.ም_____
8. ኘሮጀክቱ የተጀመረበት ቀን/ወር/ዓ.ም_____
9. ኘሮጀክቱ የሚጠናቀቅበት ቀን/ወር/ዓ.ም_____
10. የኘሮጀክቱ ተጠቃሚዎች ወንድ_____ሴት_____ድምር_____
11. የኘሮጀክቱ ኮምፖነንቶችና የተመደበላቸው ገንዘብ

ኮምፖነንት	የተመደበ ገንዘብ መጠን በብር
ጠቅላላ ድምር	

ያዘጋጁ ስም_____
የስልክ ቁጥር_____
ፊርማ_____
ቀን_____

ያረጋገጠው ባለስልጣን
ስም_____
የስልክ ቁጥር_____
ፊርማ_____

CCRDA

ቅጽ-ዓዕ2

የመያድ ዓመታዊ ዕቅድ

የመያድ ስም_____
የኘሮጀክቱ ስም_____
ኘሮጀክቱ የሚገኝበት ዞን_____
ወረዳ_____
ቀበሌ_____
ዓ.ም_____

1. የፊዚካል ሰራዎች ዕቅድ

ተራ ቁ	ኮምፖነንትና ዋና ዋና ተግባራት	መለኪያ	የኘሮጀክት ዕቅድ /ብዛት/ ለአጠቃላይ የኘሮጀክቱ ዘመን	ለዓመቱ	ግንባታው የሚገኝበት ሁኔታ	የሩብ ዓመት ዕቅድ /ብዛት/ I	II	III	IV	መግለጫ
1	ግንባታዎች									
1.1	በሂደት ላይ ያሉ ግንባታዎች									
	1.1.1									
	1.1.2									
	1.1.3									
	1.1.4									
	.									
	.									
	ድምር									
1.2	አዲስ የተጀመሩ ግንባታዎች									
	1.2.1									
	1.2.2									
	1.2.3									
	1.2.4									
	.									
	ድምር									
2	ግንባታ ያልሆኑ ሌሎች ስራዎች									
	2.1									
	2.2									
	2.3									
	2.4									
	.									
	ድምር									

*ይህ ቅጽ በአግባቡ እየተዘጋጀ እ.ኤ.አ በየዓመቱ በዲሴምበር መጨረሻ ላይ ለሚመለከታቸው መ/ቤቶች ሁሉ መቅረብ ይኖርበታል።

CCRDA

ቅጽ-ዓዕ 4

በዓይነት የሚቀርብ የምግብ ዕርዳታ ዕቅድ

የመያድ ስም_____
የፕሮጀክቱ ስም_____
ፕሮጀክቱ የሚገኝበት ዞን _____
ወረዳ_____
ቀበሌ_____
ዓ.ም_____

ተራ ቁ	የምግብ ዓይነት	መለኪያ	የምግብ መጠን					መግለጫ
			ለዓመቱ	ለየሩብ ዓመ·				
				I	II	III	IV	

* ሞኒታይዝድ/monietized/ ማይደረግ በዓይነት ቀርቦ በዓይነት የሚከፋፈለውን የምግብ ዕርዳታ ብቻ በዚህ ቅጽ ላይ መጠቀስ ይኖርበታል፡፡

CCRDA

ቅጽ-ኅዕ5

ለመያድ ኘሮደክቶት ማስፈጸሚያ ከውጭ አገር የሚገቡ ቋሚ ዕቃዎት ዕቅድ

የመያድ ስም _____
የኘሮጀክቱ ስም _____
ኘሮጀክቱ የሚገኝበት ዞን_____
ወረዳ_____ቀበሌ_____
ዓ/ም _____

ተራ ቁጥር	ከውጭ አገር የሚገቡ ቋሚ ዕቃዎች ዝርዝር			ኘሮጀክቱ ከተፈረመ ወዲህ ለኘሮጀክቱ ማስፈጸሚያ የገቡ ቋሚ ዕቃዎች		በዓመቱ እንዲገቡ በዕቅድ የተያዙ ቋሚ ዕቃዎች		መግለጫ
	የዕቃው ዓይነት	መለኪያ	ብዛት	ብዛት	ዋጋ በብር	ብዛት	ዋጋ በብር	

. ከውጭ አገር የሚገባው ቋሚ ዕቃ ለምን አገልግሎት እንደሚውል በ"መግለጫ" ላይ ይጠቀስ፡፡
. መያድ ለኘሮጀክቶቻቸው ማስፈጸሚያ ከውጭ አገር የሚገቡላቸውን ቋሚ ዕቃዎች በወቅቱ ለኘሮጀክት ሣይት ማድረስና ለዞኑ አመዝኮ ማሳወቅ ይጠበቅባቸዋል፡፡

CRDA

ቅጽ-ዓሰ 6

የኘሮጀክት ሠራተኞች ፍላጐት ፅቅድ

የመያድ ስም_____
የኘሮጀክቱ ስም_____
ኘሮጀክቱ የሚገኝበት ቦታ
ዞን_____
ወረዳ_____
ቀበሌ_____
ዓ.ም_____

ተራ ቁጥር	የኘሮጀክቱ ሠራተኞች የስራ ኃላፊነት	ሙያ	ኢትዮጵያውያን			የውጭ አገር ዜጋ			መግለጫ
			ወንድ	ሴት	ድምር	ወንድ	ሴት	ድምር	

*ይህ ቅጽ በአግባቡ እየተሞላ እ.ኤ.አ በጥር ወር ላይ ለክልሉና ለዞኑ አመዝኮ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

CRDA

ቅጽ-ሩዕአ 1

የመያድ የሩብ ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ

የኘሮጀክቱ መሠረታዊ መረጃዎች ማስፈሪያ ቅጽ

1. የኘሮጀክቱ ስም_____
2. የኘሮጀክቱ ኮድ_____
3. ዕርዳታ ሰጭ/ስም_____
4. ኘሮጀክቱ የሚገኝበት ቦታ ክልል_____
   ዞን_____
   ወረዳ_____
   ቀበሌ_____
5. አስፈጻሚ መ/ቤት(ተፈራራሚ መ/ቤቶች) _____
6. ፈጻሚ መ/ቤት _____
7. ኘሮጀክቱ የተፈረመበት ቀን/ወር/ዓ.ም_____
8. ኘሮጀክቱ የተጀመረበት ቀን/ወር/ዓ.ም_____
9. ኘሮጀክቱ የሚጠናቀቅበት ቀን/ወር/ዓ.ም_____
10. የኘሮጀክቱ ተጠቃሚዎች ወንድ_____ሴት_____ድምር_____
11. የኘሮጀክቱ ኮምፖነንቶችና የተመደበላቸው ገንዘብ

ኮምፖነንት	የተመደበ ገንዘብ መጠን በብር
ጠቅላላ ድምር	

ያዘጋጁ ስም_____
የስልክ ቁጥር_____
ፊርማ_____
ቀን_____

ያረጋገጠው ባለስልጣን
ስም_____
የስልክ ቁጥር_____
ፊርማ_____

CCRDA

ቅጽ-ሩዕአ2

የሩብ ዓመት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት

የሪፖርት ጊዜ ከ_____ወር
እስከ_____ወር_____ዓ/ም
የ_____ሩብ ዓመት

የኘሮጀክቱ ስም፡- _____
1. የኘሮጀክት ፊዚካል አፈጻጸም ሪፖርት

ተራ ቁጥር	ኮምፖነንትና ዋና ዋና ተግባራት	መለኪያ	የኘሮጀክቱ ዕቅድ		በዚህ ሩብ ዓመት		እስከዚህ ሩብ ዓመት መጨረሻ		መግለጫ
			ለዓመቱ	ለሩብ ዓመቱ	ብዛት	%	ብዛት	%	
1	**የግንባታ ሥራዎች**								
1.1	በሂደት ላይ የሚገኙ ግንባታዎች								
	1.1.1								
	1.1.2								
	1.1.3								
	.								
	ድምር								
1.2	አዲስ የተጀመሩ ግንባታዎች								
	1.2.1								
	1.2.2								
	1.2.3								
	1.2.4								
	1.2.5								
	.								
	ድምር								
2	ግንባታ ያልሆኑ ሌሎች ሥራዎች								
	2.1.1								
	2.1.2								
	2.1.3								
	2.1.4								
	2.1.5								
	.								
	ድምር								

* ይህ ቅጽ በአማባቡ እየተዘጋጀ እ.ኤ.አ. በሚቀጥለው ሩብ ዓመት ሁለተኛ ሣምንት ላይ አግባብ ላላቸው መ/ቤቶች መቅረብ ይኖርበታል፡፡
* በዚህ ቅጽ መሠረት ሪፖርት ለማቅረብ የሚያስችግሩ ሥራዎች ካሉ በተለየ ቅጽ በማዘጋጀት ከዚህ ጋር አያይዞ ማቅረብ ይቻላል፡፡

Copy

ቅጽ-ሩዕአ3

2. የኘሮጀክት ፋይናንስ አፈጻጸም ሪፖርት

የኘሮጀክቱ ስም፡- _____

የሪፖርት ጊዜ ከ_____ወር
እስከ_____ወር_____ዓ/ም
የ_____ሩብ ዓመት

ተራ ቁጥር	ኮምፖነንትና ዋና ዋና ተግባራት	መለኪያ	የኘሮጀክቱ ዕቅድ		በዚህ ሩብ ዓመት		እስከዚህ ሩብ ዓመት መጨረሻ		መግለጫ
			ለዓመቱ	ለሩብ ዓመቱ	ብዛት	%	ብዛት	%	
1	**የግንባታ ሥራዎች**								
1.1	በሂደት ላይ የሚገኙ ግንባታዎች								
	1.1.1								
	1.1.2								
	1.1.3								
	.								
	ድምር								
1.2	አዲስ የተጀመሩ ግንባታዎች								
	1.2.1								
	1.2.2								
	1.2.3								
	1.2.4								
	1.2.5								
	.								
	ድምር								
2	ግንባታ ያልሆኑ ሌሎች ሥራዎች								
	2.1								
	2.2								
	2.3								
	2.4								
	2.5								
	.								
	ድምር								

* በዓይነት የተከፋፈለ የምግብ ዕርዳታ መጠኑ በ"መግለጫ" ላይ ይስፈር፡፡
* ይህ ቅጽ በአግባቡ እየተዘጋጀ በሚቀጥለው ሩብ ዓመት ሁለተኛ ሣምንት ላይ አግባብ ላላቸውመ/ቤቶች መቅረብ ይኖርበታል፡፡
* በዚህ ቅጽ መሠረት ሪፖርት ለማቅረብ የሚያስቸግሩ ሥራዎች ካሉ በተለየ ቅጽ በማዘጋጀት ከዚህ ጋር አያይዞ ማቅረብ ይቻላል፡፡

CRDA

ቅጽ ሩዕአ4

በስራ ሂደት ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮች

የመያድ ስም_____
የኘሮጀክቱ ስም_____
ኘሮጀክቱ የሚገኝበት ቦታ፡-
ዞን_____
ወረዳ_____
ቀበሌ_____

ተራ ቁጥር	ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮች	ችግሮቹን ለመፍታት የተወሰዱ እርምጃዎች	ያልተፈቱ ችግሮችን ለመፍታት ወደፊት ሊወሰዱ የሚገባቸው የመፍትሄ ሃሳቦች	ምርመራ

CCRDA

ቀን_____

ቅጽ ኘማሪ 1

የኘሮጀክት ማጠቃለያ ሪፖርት

በኘሮጀክት ማጠቃለያ ሪፖርት ዝግጅት ወቅት ሊተኮርባቸው የሚገቡ መንደርደሪያ ነጥቦች/Terms of reference/

I. የኘሮጀክት ምልመላ /project identification/

ሀ. የኘሮጀክቱ ስም

ለ. ኘሮጀክቱ የሚገኝበት ቦታ

ሐ. ለጋሽ ድርጅት

መ. አስፈጻሚ መ/ቤት

ሰ. ፈጻሚ ድርጅት

ረ. የኘሮጀክት ወጪ /በገንዘብና በዓይነት/

II. ዓላማ/በኘሮጀክት ዶክሜንቱ በተቀመጠው መሰረት የአጭር ጊዜና የረጅም ጊዜ ዓላማዎችን ሊቀመጡ ይገባል/፡፡

III. ዝርዝር ተግባራትና የተከናወኑ ስራዎች

/ ስራዎቹ በዝርዝር መጠቀስ ይኖርባቸዋል/

ሀ. ተጠቃሚ ህዝብ ብዛት

ለ. ቀደም ሲል ከተያዘው ዕቅድ አንፃር የተከናወኑ ስራዎች/በመቶኛ ማስቀመጥ ይቻላል/

ሐ. ህይወትን ከማዳን፣ የስራ ዕድል ከመፍጠር፣ ፍትሃዊ የሀብት ክፍፍል ከማካሄድና የህዝቡን ጥሪት ከማዳበር አኳያ የተከናወኑ ተግባራት፣

መ. ከልማት ጋር ያለው ተያያዥነት

ሰ. ኘሮጀክቱ ያስገኘው ተጨባጭ ውጤት /Impact/

ረ. ዘላቂነትን ከማረጋገጥ አንፃር የተወሰደ እርምጃ

ሸ. የህብረተሰቡ የተሳትፎ ደረጃ

CCRDA

IV. *የሀብት አጠቃቀም*

/በዝርዝር መቅረብ ይኖርበታል/

ሀ. ቀደም ሲል ከተያዘው ዕቅድ አንፃር የገንዘብ ወጪ አጠቃቀም

ለ. የማቴሪያል አጠቃቀም

ሐ. ወደፊት ኘሮጀክቱን ለሚረከበው አካል ንብረት የማስተላለፍ ሁኔታ

መ. በኘሮጀክቱ የነበረ የሰው ኃይል ብዛት /ኢትዮጵያውያን የውጭ አገር ዜጋ/ ክህሎት ያላቸው በከፊል ያላቸውና የሌላቸው/

ሰ. ከህብረተሰቡና ከሌሎች ድርጅቶች ተገኝቶ በጥቅም ላይ የዋለ ሀብት

ረ. በጥቅም ላይ ያልዋለ ወይም በተጨማሪ በጥቅም ላይ የዋለ ሀብት

V. *የኘሮጀክቱ ማኔጅመንት*

ሀ. ከአስፈጻሚ መ/ቤቶች ማለትም ከአመዝኪ፣ከሴክተር መ/ቤቶችና በተዋረድ ከሚገኙ መስተዳድር አካላት ጋር ያለው የስራ ግንኙነት፣

ለ. ከህብረተቡ ጋር ያለው የስራ ግንኙነት

ሐ. ያጋጠሙ ችግሮችና ችግሮችን ለማስወገድ የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች

መ. ማኔጅመንቱን በተመለከተ ሌላ የሚጠቀስ ነገር ካለ ይጠቀስ

VI. ማጠቃለያና የመፍትሄ ሃሳቦች

ሀ/ በመንግሥት አካላት በየደረጃው መወሰድ የሚገባቸው ፣

ለ/ በመያድ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎች፣

ሐ/ የኘሮጀክቱን ቀጣይነት/sustainability/ የሚያረጋግጡ ነጥቦችን ማካተት፣

CCRDA

- ከላይ በተቀመጡት ነጥቦች መሰረት የሚዘጋጀው የኘሮጀክት ማጠቃለያ ሪፖርት ኘሮጀክቱ ባለቀ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለክልሉና ለዞኑ አመዝኪ መቅረብ ይኖርበታል።

ቅጽ-አሪ1

የአዲት ማጠቃለያ ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ

1. የድርጅቱ ስም _____
2. አዲት አድራጊው ድርጅት ስም/Audit firm/ _____
3. አዲት የተደረገው ፕሮጀክት ስም _____
4. ፕሮጀክቱ የሚገኝበት ዞን _____
   ወረዳ _____
   ቀበሌ _____
5. አዲት የተካሄደበት ዓ/ም _____
6. በአዲት ሪፖርቱ መሠረት፡-
   - በዓመቱ ለፕሮጀክቱ ማስፈጸሚያ ድርጅቱ ገቢ ያደረገው የገንዘብ መጠን
     በብር _____
   - በጉድለት የታየ የገንዘብ መጠን
     በብር _____
   - የታዩ የአሠራር ችግሮች
     _____
     _____
     _____
     _____
     _____
   - ወደፊት መደረግ ያለባቸው ማስተካከያዎች
     _____
     _____

* ይህ ማጠቃለያ ሪፖርት በአዲት አድራጊው ከቀረበው ዝርዝር የአዲት ሪፖርቱ በመነሣት የሚዘጋጅና ከዋናው የአዲት ሪፖርት ጋር እ.ኤ.አ. በየዓመቱ በጥር ወር ላይ ለክልሉና ለዞኑ አመዝኮ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

CCRDA

ቅጽ-ኢሪ 1

ኢንቨንተሪ ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ

የድርጅቱ ስም_____
የፕሮጀክቱ ስም_____
ፕሮጀክቱ የማገኝበት ዞን_____
ወረዳ_____
ቀበሌ_____
ኢንቨንተሪ ሪፖርቱ የቀረበበት ዓ.ም_____

የዕቃው ዓይነት	መለኪያ	ብዛት	ካለፈው ዓመት ጋር ሲነፃፀር የታየ ልዩነት		በመብለጥም ሆነ በማነስ ለታዩት ልዩነቶች ምክንያቶች
			በመብለጥ ብዛት	በማነስ ብዛት	
1.ቋሚ ዕቃዎች 1.1 1.2 1.3 1.4 1.5 . . . . 2. አላቂ ዕቃዎች 2.1 2.2 2.3 2.4					

COPY